Ambasáid na hÉireann
Embassy of Ireland
የስርዓተ ፆታና ታዳጊነት፡
አለማቀፋዊ መረጃ


ትምህርቷን አየተከታተለች ጎን ለጎን አናቷን በቤት ስራ የምትረዳ የአሰር አመት ልጃገረድ፣ አፋር ክልል፣ ኢትዮጵያ © ናታሊ በርትራምስ / ጌጅ 2014 ዓ. ም.

# በኢትዮጵያ አርብቶ አደር የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን የማስቀረት ፈጣን ጉዞ፡ የፖሊሲና ፕሮግራም ቅድሚያዎች

ከፍያለው እንዳለ፣ ኒኮላ ጆንስ፣ ኤልሳቤት ፕሪስለር-ማርሻል፣ ጣሰው ወልደሃና፣ ወርቅነህ ያደቴ[1]፣ አብዲላሂ አብዲሰላም፣ አብርሀም አለሙ፣ ይታገሱ ገበየሁ፣ ኪያ ገዛኸኝ፣ ሮብሃ ሙርሃ፣ አቤል ተስፋዬ፣ ካሳሁን ጥላሁንና ፍጹም ወርቅነህ[2]

## አጠቃላይ እይታ

የህፃናት ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት (ብልት መቁረጥ) የዕድሜ ልክና ትውልድ ተሻጋሪ በርካታ መዘዝ ያስከትላሉ። በመሆኑም እነዚህን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መዋጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ የልማት ቀዳሚ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። በዘላቂ ልማት ግብ 5 (የፆታ እኩልነት) ከተቀመጡት ግቦች ውስጥ በንዑስ ግብ 5.3.1 (የህፃናት ጋብቻን ማስወገድ) እና 5.3.2 (የሴት ልጅ ግርዛትን ማስወገድ) የተጠቀሱት ሁለቱ በቀጥታ እነዚህን ተግባራት ይመለከታሉ። ኢትዮጵያ ባለፉት 20 ዓመታት ውስጥ የህፃናት ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን በመዋጋት ረገድ ፈጣን እድገት አሳይታለች (UNICEF, 2020)። ይህም ሆኖ አሁንም በአለም አቀፍ ደረጃ ያለዕድሜያቸው ያገቡ ልጃገረዶች ከፍተኛ ቁጥር ካሉባቸው ከመጀመሪያዎቹ አምስት ሀገራት አንዷ ነች። በተጨማሪም፣ በምስራቅና በደቡብ አፍሪካ ካሉ ሀገራት ለአንድ ሀገር ፍፁም ትልቅ ቁጥር የሚባለውን ወደ 25 ሚሊዮን የሚገመቱ የሴት ልጅ ግርዛት ያጋጠማቸው ልጃገረዶችና ሴቶች ይገኙባታል (ibid.)።

1 የመጀመሪያዎቹ አምስት ደራሲዎች ሁሉም የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቡን መሠረት በማድረግ መረጃ በመተንተን ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉ ናቸው።
2 ሁለተኛው የደራሲዎች ቡድን ደግሞ በመረጃ ስብሰባና በመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ትንተና ላይ የተሳተፉ ናቸው። ሙሉ የምስጋና ዝርዝር በዋናው ሪፖርት ውስጥ ተካቷል።

የዋቢ ፅሁፍ ጥቆማ፡ Endale, K., Jones, N., Presler-Marshall, E., Woldehanna, T., Yadete, W., Abdisalam, A., Alemu, A., Gebeyehu, Y., Gezahegne, K., Murha, R., Tesfaye, A., Tilahun, K. and Workneh, F. (2022) 'Fast-tracking progress towards eliminating FGM/C and child marriage in pastoralist Ethiopia: priorities for policy and programming'. Policy brief. London: Gender and Adolescence: Global Evidence.

በመላ አገሪቱ የህፃናት ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት መጠን ይለያያል። ይህም በአንዳንድ ክልሎች ከፍተኛ መቀነስ ሲታይ በሌሎች ደግሞ ገና መሻሻል አላሳየም። የአፋር እና የሶማሌ ክልል መንግስታት በኢትዮጲያ ከፍተኛው የሴት ልጅ ግርዛት ያካሄዱ ከ15-49 እድሜ ያላቸው ሴቶች (91% እና 99% በቅደም ተከተል) የሚገኙባቸው ናቸው። በአፋር ክልል የመጀመሪያ ጋብቻ የፈጸሙ ሴቶች አማካይ ዕድሜ (16.4 ዓመት) በአገሪቱ ከተመዘገበው አማካይ ዕድሜ (17.5 ዓመት ጋር ሲነጻጸር) ያነሰ ነው (CSA እና ICF, 2017)። በኢትዮጵያ የህፃናት ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም በተዘጋጀው ሀገራዊ ፍኖተ ካርታ (2020-2024) እንዲሁም ሀገሪቱ የዘላቂ ልማት ግቦችን (SDG) ለማሳካት ባላት ቁርጠኝነት መሰረት በአየርላንድ መንግስት አዲስ የምርምር ፕሮጀክት ተጀምሯል። የፕሮጀክቱ ዓላማ በአሁኑ ወቅት በአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ የሚስተዋለውን የሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ ያለበትን ደረጃና አነሳሽ ምክንያቶች ለማሳየት፣ እንዲሁም በጊዜ ሂደት፣ በሴቭ ዘቸልድረን የተተገበረውን ሁለገብ ፕሮግራም ለመገምገምና የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን ለማስቀረት ነው (ሣጥን 1ን ይመልከቱ)።

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ በ2022 መጀመሪያ ላይ ከተደረጉ በቅይጥ ዘዴ ጥናት የተገኙ ግኝቶችን ባጭሩ ያስቀምጣል (Endale et al., 2022 ይመልከቱ)። በተጨማሪም የሀገራዊ ፍኖተ ካርታ ትግበራን ጨምሮ የጥናት ግኝቶቹ ለፖሊሲና ለፕሮግራም ቀረጻ ያላቸውን አንድምታ ያስቀምጣል። የዚህ ዙር ጥናት እንደ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል እንደመሆኑ መጠን የተቀመጡት ምክረሀሳቦች ከሴቭ ዘቸልድረን ፕሮግራም ተፅእኖ ትንተና የተወሰዱ እንዳልሆኑ መታወቅ አለበት። ይልቁንም ምክረሃሳቦቹ በሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ ደንቦችና ልማዶች ላይ በተደረገው ሰፊ ጥናት ግኝቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

## የጥናቱ ዳራ

በኢትዮጵያ ከ2000 እና 2005 ጀምሮ የህፃናት ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት ህገ ወጥ ድርጊቶች ናቸው። መንግሥት እነዚህን ሁለቱንም ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለማስቀረት ያደረገው ጥረት ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ በአገራዊ የፖሊሲ ማዕቀፎች ውስጥ ተንጸባርቋል። በ2013 የሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ሚኒስቴር በሴቶችና ህጻናት ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ብሄራዊ ስትራቴጂና የድርጊት መርሃ ግብር አውጥቷል። ይህን ተከትሎ በ2025 የህፃናት ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም በ2019 ብሄራዊ ፍኖተ ካርታ ዘርግቷል።

በእነዚህ ጠንካራ የህግና የፖሊሲ ማዕቀፎች የተደገፈችው ኢትዮጵያ በአገር አቀፍ ደረጃ የህፃናት ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን በማስቀረት ረገድ ጉልህ እድገት አሳይታለች። እንደ ኢትዮጵያ የስነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ (EDHS)፣ በ2000 በጉርምስና ዕድሜ ላይ ከሚገኙት ልጃገረዶች 14 በመቶ የሚሆኑት ያገቡት 15 ዓመት ሳይሞላቸው ሲሆን 49 በመቶ የሚሆኑት ወጣት ሴቶች ደግሞ ያገቡት 18 ዓመት ሳይሞላቸው ነው (CSA እና ORC Macro, 2001)። ይህ አሀዝ በ2016 ዓ/ም በቅደም ተከተል ወደ 6% እና 40% ዝቅ ብሏል (CSA እና ICF፣ 2017)። በ2000 የተደረገው ጥናት እንዳመለከተው ከ15-19 ዕድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ታዳጊ ልጃገረዶች መካከል 71% የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛት ተፈፅሞባቸዋል (CSA and ORC Macro, 2001)። ይህ አሀዝ በ2016 ወደ 47% ወርዷል (CSA እና ICF፣ 2017)። ይሁን እንጂ፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ይህ መሻሻል በሁሉም ክልሎች ሲታይ እኩል አይደለም። በኢትዮጵያ ታዳጊ በሚባሉት የአፋርና ሶማሌ አርብቶ አደር ክልሎች የሴት ልጅ ግርዛት መጠን የማይለዋወጥ ሲሆን የህፃናት ጋብቻ መጠን ደግሞ እየጨመረ ነው (CSA and ORC Macro, 2001; CSA and ICF, 2017; Elezaj et al., 2019)። የሁለቱም ክልል መንግስታት የሴት ልጅ

### ሳጥን 1: በአፋርና በሶማሌ ክልሎች የህፃናት ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን ለመቀነስ ሴቶች እና ልጃገረዶችን ማብቃት፡ አዲስ የፕሮግራሚንግ ኢኒሺየቲቭ

የአየርላንድ መንግስት ከሴቭ ዘ ቸልድረን ጋር በመተባበር ‹‹በኢትዮጵያ ቆላማ አካባቢዎች የሚገኙ ሴቶችንና ልጃገረዶችን መደገፍ እና ከጥቃትና ብዝበዛ ነጻ ሆነው ጤናማና ፍሬያማ ኑሮን ይኑሩ›› በሚል የአምስት ዓመት የ7.8 ሚሊዮን ዩሮ ፕሮግራም ድጋፍ ያደርጋል። የፕሮግራሙ ዓላማ ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ አቅም እንዲያገኙ ማድረግ እንዲሁም ጎጂ የሆኑ የስርዓተ ጾታ ደንቦችና ልማዶች በተለይም የሴቶችን ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ በህይወታቸው ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ተፅዕኖ መቀነስ ነው።

ይህ ፕሮግራም በአፋር ክልል በሁለት ዞኖች በሚገኙ በሶስት ወረዳዎች (በዞን 1 አይሳይታና ሰሞሮቢ ወረዳዎች፣ በዞን 5 ሀደለላ ወረዳ) እንዲሁም ሶማሌ ክልል ውስጥ በሚገኙ ሁለት ዞኖች (በጃራር ዞን ዳሮር ወረዳ፣ በፋፋን ዞን በሐርሸንና በጎልጃኖ ወረዳዎች) ባሉ ሶስት ወረዳዎች በመተግበር ላይ ይገኛል። ስድስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች በሴቶችና በልጃገረዶች ላይ ብቻ ሳይሆን በአካባቢው በሚገኙ አገልግሎት ሰጪዎች፣ በወንዶች ልጆችና አዋቂ ወንዶች፣ እና በማህበረሰቦች ላይም ያተኩራሉ። የስራ መስኮቹ ደግሞ፦ (1) የገንዘብና የንብረት ዝውውሮች፣ የቁጠባና የብድር እድሎችን ማግኘትና የራስን ስራ ለመፍጠር ድጋፍ ማድረገን ጨምሮ የኢኮኖሚ አቅም ማጎልበት፣ (2) ከትምህርት ውጪ ያሉ ልጃገረዶች ትምህርት ቤት እንዲመዘገቡ ለመርዳት የቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግና በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ማጠናከሪያ ስልጠና መስጠት፣ (3) ሴቶችና ልጃገረዶች ለመብታቸው በብቃት መሟገት እንዲችሉ የአመራር ስልጠና መስጠትና የልጃገረዶች ክለቦችን ማቋቋምን ጨምሮ የሴቶች እና የልጃገረዶች ተሳትፎ፣ (4) ከጥቃት የተረፉት ከጥቃት እንዲጠበቁና የወሲባዊ እና ሥነ ተዋልዶ ጤና አገልግሎቶችን እንዲያገኙ መደገፍን ጨምሮ ከሥርዓተ-ፆታ ጥቃት መከላከል፣ (5) ከአዋቂ ወንዶችና ወንዶች ልጆች ጋር በወንዶች በተያዙ ቦታዎች ላይ መስራትን ጨምሮ የማህበረሰብ ተሳትፎ ማድረግ፣ እንዲሁም በጎሳና በሃይማኖት መሪዎች የሚመሩ የማህበረሰብ ውይይቶችን ማድረግ፣ እና (6) ለአካባቢ አመራሮችና አገልግሎት ሰጪዎች ስልጠና መስጠትን ጨምሮ የአቅም ግንባታና የማስተባበር ስራ ናቸው።

ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን የሚከለክለውን ብሄራዊ የቤተሰብ ህግ ገና ሊያፀድቁ ነው። በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችና ወግ አጥባቂ የስርዓተ-ፆታ ደንቦች መካከል ያለው ትስስር እንዳለ ሆኖ እነዚህ ክልሎች ልጃገረዶች እና ሴቶች በተለይ የመማርና ስራ የመቀጠር እድላቸው ውስን የሆነባቸው ክልሎች መሆናቸው አያስገርምም (Presler-Marshall et al., 2022)። የኢትዮጵያ መንግስትና አጋሮቹ በቅርቡ በታዳጊ ክልሎቹ የሚስተዋሉትን እነዚህን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት በዘላቂ ልማት ግቦች ማዕቀፍ በተቀረጹ ኋላቀርነት ስጋት ላይ ያተኮሩ ጥረቶችን አጠናክረው ቀጥለዋል።

## የጥናቱ ዘዴ

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ የተወሰደው በአፋር እና በሶማሌ ክልሎች የህፃናት ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት ያለበትን ደረጃና አነሳሽ ምክንያቶችን በመዳሰስ በቀይጥ የጥናት ዘዴ የመነሻ ግምገማ ከተገኙ ውጤቶች ነው። መነሻው በ2022፣ 2024 እና 2026 ውስጥ ሶስት ዙር መጠናዊና ዓይነታዊ መረጃ አሰባሰብን ያካተተ የረጅም ጊዜ የምርምር ግምገማ አካል ነው። የጥናት ቡድኑ የሚመራው በስርዓተ ፆታና ታዳጊነት ጀንደር ኤንድ አዶለሰንስ፡ ግሎባል ኤቪደንስ (GAGE) ፕሮግራምና ኦዲአይ (ODI) ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎችና ከኩዌስት ኮንሰልቲንግ ጋር በመተባበር ነው። ቡድኑ የአፋርና የሶማሌ ክልል ተመራማሪዎችን ያካትታል።

የመጠናዊ ናሙናው ለሁለቱ ክልሎች እኩል የተከፈሉ 2,042 አባወራዎችን (ከ10-19 አመት እድሜ ያላቸው 2,042 ታዳጊዎች እና 2,042 አሳዳጊዎችን) ያካትታል። የናሙና መጠኑ የሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ አመላካቾችን ቀናሽ ለመለየት በ10 በመቶ ነጥብ፣ በ95% ፓወር ተወስኗል። ከጥናቱ የሚያቋርጡ ተሳታፊዎችን ለማካካስ የናሙና መጠኑ በ15% እንዲጨምር ተደርጓል። በየክልሉ ፕሮግራሙ በሚተገበርባቸው 9 ቀበሌዎች (ማህበረሰቦች) እና ምንም አይነት ፕሮግራም በ ሌላቸው 9 ቀበሌዎች መረጃ ተሰብስቧል። ሁሉም የገጠር ቀበሌዎች ቢሆኑም አንዳንዶቹ ከሌሎቹ በጣም ርቀው ይገኛሉ። የዓይነታዊ ናሙናው በተናጠልና በቡድን ቃለመጠይቆች የተሳተፉትን 295 ታዳጊዎችንና 166 አሳዳጊዎቻቸውን ያካትታል። በተጨማሪም በቁጥር 84 ከሚሆኑ የቀበሌ (ማህበረሰብ)፣ የወረዳና የክልል የመንግስት ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ አገልግሎት ሰጪዎች እና የሴቶች ዘ ችልድረን የወረዳና የክልል ሰራተኞች ቁልፍ የመረጃ ሰጪ ቃለ መጠይቆችን አካቷል።

## ቁልፍ ግኝቶች

### ትምህርት

በሶማሌ ክልል ከተሳተፉት ወጣቶች መካከል ሁለት አምስተኛ (39%) የሚሆኑት እና በአፋር ክልል ከተሳተፉት 27% የሚሆኑት በጭራሽ ትምህርት ቤት እንዳልገቡ ተናግረዋል። ከነዚህም መካከል አብዛኞቹ ልጃገረዶች ናቸው። በሶማሌ ክልል 43% የሚሆኑት ልጃገረዶች 27% ከሚሆኑት ወንዶች ልጆች ጋር ሲነጻጸሩ በጭራሽ ትምህርት ቤት ገብተው አያውቁም። በአፋር ክልል የፆታ ልዩነቱ አነስተኛ ቢሆንም ወንዶች (27%) አሁንም

> **ቁልፍ ግኝት:**
>
> - በጥናቱ ከተካተቱት ታዳጊዎች መካከል አንድ ሶስተኛ የሚጠጉት ትምህርት ቤት ገብተው አያውቁም፤ ትምህርት ቤት ከገቡት መካከልም አብዛኞቹ ትምህርት የሚጀምሩበት ዕድሜ የተላለፋቸው ናቸው።
> - የልጃገረዶች ትምህርት የማግኘት ዕድል በተለይ በሶማሌ ክልል ከወንዶች የከፋ ነው። ይህም የሆነው በወግ አጥባቂ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች፣ በትምህርት ቤት ያለው ደካማ የንጽህና መጠበቂያ አቅርቦትና ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ በመንገድ ላይ በሚያጋጥማቸው የደህንነት ስጋት ምክንያት ነው።

ከሴቶች (32%) 5 በመቶ ትምህርት ቤት የመግባት እድላቸው ከፍ ያለ ነበር። ልጃገረዶች ከወንዶች ልጆች የበለጠ ትምህርታቸውን ያቋረጡ ነበሩ። ይህ ጥናት በሚካሄድበት ወቀት ትምህርት ቤት የገቡት ወጣቶች ሁሉም ማለት ይቻላል ትምህርት የሚጀምሩበት ዕድሜ የተላለፋቸው ነበሩ።

የዓይነታዊ ጥናቱ በትምህርት ተደራሽነት ላይ በርካታና እርስ በርስ የሚጋጩ እንቅፋቶችን ለይቷል፤ ውጤቱ በሁሉም ክልሎች በአብዛኛው ተመሳሳይ ነበር። ይህም ለወንዶቹም ለሴቶቹም ረጅም ሰዓት የሚወስድ የትምህርት ቤት ጉዞ (በተለይ በመለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች)፣ የመጠጥ ውሃ ችግር ያለባቸው ትምህርት ቤቶች (በተለይ በበረሃማ አካባቢዎች ከተቆረቆሩ ረጅም ጊዜ የሆናቸው)፣ ከትምህርት ቤት የሚቀሩ መምህራን፣ እና ዝቅተኛ የትምህርት ጥራትን ያካትታል። ልጃገረዶች ተጨማሪ መሰናክሎች ያጋጥሟቸዋል። እነዚህም ዘግይቶ ትምህርት መግባትን፣ አዘውትሮ ከትምህርት ቤት መቅረትና ትምህርት ማቋረጥን የሚያስከትሉ ከባድ የቤት ውስጥ ኃላፊነቶችን፤ በትምህርት ቤቶች የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ ምርቶችና የግል መጸዳጃ ቤት /መታጠቢያ አቅርቦት ውስንነትን፤ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጓጓዣ እጥረትን ያጠቃልላል። የህፃናት ጋብቻ በተለይም በከፍተኛ የመጀመሪያ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለልጃገረዶች ትምህርት ማቋረጥ ወሳኝ ምክንያት ሆኖ ተገኝቷል። የሶማሌ ክልል ምላሽ ሰጪዎች እንደገለፁት ቀደም ባሉት ጊዜያት የትምህርት ቤት ምገባ ትምህርት ቤት የሚገቡ ልጆችን ያበረታታ ነበር፤ ነገር ግን ከተቋረጠ በኋላ ትምህርት የሚገቡ ተማሪዎች ቁጥር መቀነስ ጀምሯል። መላሾቹ አክለውም ብዙ ወላጆች ሴቶች ልጆቻቸውን ትምህርት ቤት የማይልኩት ከወንዶች ጋር ተገቢ ያልሆነ ጾታዊ ግንኙነት ሊፈጽሙ ይችላሉ በሚል ፍራቻ ነው።

### የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት

በአፋር (44%) እና በሶማሌ (31%) ብዙ ቁጥር ያላቸው ሴት አሳዳጊዎችዎች እራሳቸውን እንደ ቤት ሰሪ አድርገው ይቆጥራሉ፤ ወንዶች (በአፋር 72%፣ በሶማሌ 72%) ከሴቶች (በአፋር 49%፣ በሶማሌ 40%) የበለጠ እርሻ (የከብት እርባታ እና ሰብል ማምረት) ተቀዳሚ ተግባራቸው እንደሆነ ይገልጻሉ። በወንዶችና በሴቶች ተቀዳሚ ተግባራት ላይ የሚታየው ልዩነት በቤተሰባቸው መተዳደሪያ ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። በአፋር፣ በሴት

## ቁልፍ ግኝቶች:

- ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ራሳቸውን እንደ ‘ገቢ ፈጣሪ’ የመመልከት ዕድላቸው አነስተኛ ነው፤ ያላቸው ትርፋማ ቋሚ ሀብትም ጥቂት ነው፡፡
- የሶማሌ ክልል ሴቶች ከአፋር ክልል ሴቶች የበለጠ የተለያየ መተዳደሪያ አላቸው፡፡
- ሴቶች በገንዘብ ነክ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያላቸው ተሳትፎ በወንዶች እይታ በተለይም በአፋር ክልል ከወንዶች ያነሰ ነው፡፡
- የሶማሌ ሴቶች ከአፋር ሴቶች በበለጠ ራሳቸውን ችለው በገንዘብ ላይ ውሳኔ መስጠት እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡

እማዋራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች መተዳደሪያቸው በወንድ አባወራ ከሚተዳደሩ ቤተሰቦች የበለጠ በከብት እርባታ (77% ከ 69%) እና በጥቃቅን ንግድ (6% ከ 1%) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በሰብል እርሻ ላይ የመሰማራት እድላቸው አነስተኛ ነው (12% ከ 22%)፡፡ በሱማሌ ክልል ያለው ሁኔታ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ በሴት እማዋራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች መተዳደሪያቸው (23%) በወንድ አባወራ ከሚመሩ ቤተሰቦች (14%) ጋር ሲነጻጸር የበለጠ በጥቃቅን ንግድ ከላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ ነገር ግን በሰብል እርባታ (22% ከ 19%) እና በከብት እርባታ (38% ከ 43%) የመተዳደር እድላቸው ተቀራራቢ ነው፡፡ በሁለቱም ክልሎች በሴት እማዋራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች የመሬት ባለቤትነት በወንድ አባወራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ከሚይዙት በግምት ግማሽ የሚሆነውን ነው፡፡ ያላቸውም የሁሉም ዓይነት የከብት ብዛት ያነሰ ነው፡፡

የሴቶች በገንዘብ ላይ የመወሰን ዕድል እንደየ ክልሉ የሚለያይ ቢሆንም በአጠቃላይ ከወንዶች ያነሰ ነው፡፡ በአፋር፣ በግምት ሦስት አራተኛ የሚሆኑት ሴቶች ከባሎቻቸው እኩል እንደሚወስኑ ሪፖርት አድርገዋል፡፡ በሌላ በኩል በሶማሌ ክልል በግምት አራት አምስተኛ የሚሆኑ ሴቶች ከባሎቻቸው ውጪ ብቻቸውን በገንዘብ ላይ እንደሚወስኑ ገልጸዋል፡፡ በወሳኝነት፣ የዳሰሳ ጥናቱ እንደሚያሳየው በሁለቱም ክልሎች የሴቶች በገንዘብ ነክ ውሳኔዎች ላይ ያላቸው ተሳትፎ በወንዶች ሲገለጽ ሴቶች ራሳቸው አለን ብለው ከሚያስቡት በጣም ያነሰ ነው፡፡

የዓይነታዊ የጥናት ግኝቶቻችን የዳሰሳ ጥናቱ ያልዳሰሳቸውን ጉዳዮች ያብራራሉ፡፡ በአፋር ክልል፣ ምላሽ ሰጪዎች እንደገለፁት ወንዶች ትላልቅ ከብቶችን (ላሞችን፣ በሬዎችንና ግመሎችን) የመሸጥ ሃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ ሴቶች ደግሞ ትናንሽ የቁም ከብቶችን የመሸጥ መብት እንዳላቸውና ከነሱ የሚገኘውን ትርፍ መቆጣጠር እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡ ሴቶች የማገዶና የከሰል ሽያጭን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር የሚያገኙትን ገንዘብ ለቤተሰብ ወጪ ያውላሉ፡፡ የብድርና የቁጠባ ባህሉ ጠንካራ በሆነባቸው እንደ አይሳይታ ወረዳ ባሉ አካባቢዎች አብዛኛው የማህበረሰብ አቀፍ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ሴቶች ናቸው፡፡ በሱማሌ ክልል፣ ሴቶች ለቤተሰባቸው መደበኛ ገቢ የሚያስገኙትን አነስተኛ የቁም እንስሳትን መሸጥና መቼ እንደሚሸጡ መወሰን ብቻ ሳይሆን ከሽያጩ የሚገኘውን ገቢ ከባሎቻቸው ጋር እንዲካፈሉ አይገደዱም፡፡ የሚገርመው ነገር ወንዶች የሚያገኙትን ገቢ ለሚስቶች ማካፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሴቶች በገንዘብ ነክ ንብረቶች ላይ ያላቸው ቁጥጥር በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ትልቅ አንድምታ አለው፡፡ ይኸውም እናቶች ሴት ልጆቻቸውን እንዲገረዙ ማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም ባሎቻቸው በሴት ልጅ ግርዛት ባይስማሙ እንኳን የባሎቻቸውን ተቃውሞ ወደ ጎን በመተው ሴት ልጆቻቸውን ለማስገረዝ አቅም ይሰጣቸዋል፡፡



የጤና ባለሞያ በመሆን ማህበረሰቧን ስለማገልገል ማለም፡ ታዳጊ ልጃገረድ ከሶማሊ ክልል፤ ኢትዮጵያ © ዩኒሴፍ ኢትዮጵያ / 2008/ ቢንድራ

## የሴት ልጅ ግርዛት ሁኔታና አነሳሽ ምክንያቶች

የጥናት ግኝታችን እንደሚያሳየው በየክልሎቹ አብዛኞቹ በጥናቱ ናሙና ውስጥ የተካተቱት ከ10-19 አመት እድሜ ያላቸው ልጃገረዶች ግርዛት ተፈፅሞባቸዋል፡፡ ልማዳዊ ድርጊቶቹ በጣም የተለያዩ በመሆናቸው በጥንቃቄ የተዘጋጀ የማስተካከያ እርምጃ የሚያስፈልግ መሆኑን ያመላክታሉ፡፡

### ቁልፍ ግኝቶች:

- በአፋር ልጃገረዶች በጨቅላነታቸው ብልታቸውን ይቆረጣሉ፡፡ በሶማሌ በልጅነት ዕድሜያቸው መገባደጃ ላይ አንዳንዱ ልጃገረዶች በሚያስቀምጡት ጊዜ ይቆረጣሉ፡፡
- የሴት ልጅ ግርዛት መደረግ ስላለበትና መቼ እንደሚደረግ የመጀመሪያ ውሳኔ ሰጪዎቹ እናቶች ናቸው፡፡
- አብዛኞቹ ልጃገረዶች በባህላዊ ብልት ቆራጮች የተገረዙ ሲሆን በተለይ በሶማሌ ክልል የሕክምና ከትትል የሚደረግላቸው እንዳሉ በቂ ማስረጃ አለ፡፡
- በሁለቱም ክልሎች፣ ለሴት ልጅ ግርዛት ዋና ምክንያት የባህል ማንነት መለያ መሆኑን የጥናት ተሳታፊዎቹ ይገልጻሉ፡፡
- በሶማሌ ክልል ያሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች ከአፋር ተሳታፊዎች ይልቅ የሴት ልጅ ግርዛት ሃይማኖታዊ ግዴታ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡
- የሴት ልጅ ግርዛት ከሚያስከትለው ጉዳት ይልቅ በዋነኛነት የሴት ልጆችን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት መቆጣጠርና ባል ማግባት መቻላቸውን የማረጋገጥ ጥቅማጥቅሞች እንዳሉት የጥናቱ ተሳታፊዎች አስረድተዋል፡፡
- የሴት ልጅ ግርዛት ወንጀል ስለመሆኑ ያለው የህግ እውቀት በአጠቃላይ ዝቅተኛ ነው፡፡ በሶማሌ ያሉ አሳዳጊዎች ስለ ህግ ያላቸው ትክክለኛ እውቀት አፋር ክልል ካሉት ያነሰ ነው፡፡ በሶማሌ ክልል የህግ ግንዛቤን ማሳደግ የሚደረገውን ድጋፉ ሊቀንስ ይችላል፡፡
- በሴት ልጅ ግርዛት ላይ የሚደረገው ድጋፍ ግርዛት በሚያስከትለው ጉዳት ላይ ባለው ግንዛቤና ጥቅሞቹ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ግዴታዎች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡
- የሴት ልጅ ግርዛት የአንድ ጊዜ ክስተት ሳይሆን የህይወት ዘመን ህመምና የስሜት መቃወስን ያስከትላል፡፡
- በሶማሌ ክልል ያልሆነ፣ ነገርግን በአፋር ልጃገረዶችን ማስተማር ለሴት ልጅ ግርዛት የሚደረጉ ድጋፎችን ለመቀነስ ተስፋ ሰጭ ስልት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ሴቶችን በኢኮኖሚ ማጎልበት ለድርጊቱ የሚደረገውን ድጋፍ ይጨምራል፡፡

በአፋር ክልል፣ ስለ ሴት ልጅ ግርዛትን ሰምተው ከነበሩት 96% ከሚሆኑት ልጃገረዶች ውስጥ 97% የሚሆኑት በአብዛኛው በአንድ አመት እድሜያቸው ብልታቸውን ተቆርጠዋል፡፡ የግርዛቱን አይነት በተመለከተ፣ 83% የሚሆኑት እነዚህ ልጃገረዶች ብልታቸው ተሰፍቶ ጠባሳ እንዳወጣባቸው ተናግረዋል፡፡ ቀሪዎቹ ልጃገረዶች ደረጃ 2 (14%) ወይም ደረጃ 1 (3%) የግርዛት ዓይነት እንደተፈጸመባቸው ገልጸዋል [3]፡፡ ባህልና ኃይማኖትን ለመለየት አስቸጋሪ መሆኑን በመጥቀስ በተለይ በአሁኑ ሰዓት የመጤ ባህሎች መጠን እየጭመረ በመምጣቱ በጥናታችን የተካተቱ የአፋር ልጃገረዶች በማህበረሰባቸው ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት ዋና አነሳሽ ምክንያቶች የባህል ማንነት (65%) እና ሃይማኖት (21%) መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በሶማሌ ክልል ከ10-19 አመት እድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙት በጥናቱ ከተሳተፉ ልጃገረዶች መካከል 78% የሚሆኑት የሴት ልጅ ግርዛትን ሰምተው እንደሚያውቁ የገለፁ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 72% የሚሆኑት ብልታቸውን መቆረጣቸውን አምነዋል፡፡ የሴት ልጅ ግርዛት ያካሄዱ መሆኑን ያመኑ ልጃገረዶች ብልታቸውን የተቆረጡት በአማካይ በ9 አመት እድሜያቸው ሲሆን አንድ ሶስተኛ የሚሆኑት በጊዜው የተወሰነ አስተያየት እንደነበራቸው ተናግረዋል፡፡ ከአፋር ጋር በሚመሳሰል መልኩ የባህል ማንነት (54%) እና ሀይማኖት (33%) የድርጊቱ ዋነኛ አነሳሽ ምክንያቶች መሆናቸውን ተሳታፊ ልጃገረዶቹ አመልክተዋል፡፡ በሶማሌ ክልል የሴት ልጅ ግርዛት ስርጭት መጠን ከአፋር ክልል አንፃር ሲታይ በጣም ያነሰ ብቻ ሳይሆን ከ15-19 እድሜ ክልል ውስጥ ከነበሩት ልጃገረዶች 95% ብልታቸው የተቆረጠ ነበር ተብሎ ሪፖርት ከተደረገው ከ2016ቱ የኢትዮጵያ የስነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ (EDHS) ያነሰ ነው፡፡ ይህ ግን መሻሻልን ያሳያል ተብሎ ሊወሰድ አይገባም፡፡ ይልቁንም፣ የሴት ልጅ ግርዛት እንዴት እንደሚተገበርና ልዩነቶችን መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑንና የተለያዩ ናሙናዎችን ማወዳደር ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በሶማሌ ክልል ያሉ ልጃገረዶች እስከ ጋብቻ ጊዜ በየትኛውም እድሜ ብልታቸውን ሊቆረጡ ስለሚችሉ በጥናቱ የተሳተፉ አብዛኛዎቹ ልጃገረዶች መረጃ በሚሰበሰብበት ጊዜ ዕድሜያቸው በአማካይ 13 አመት ብቻ የነበሩ ልጃገረዶች በቀጣዮቹ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ሊቆረጡ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በሱማሌ ክልል ባደረግነው ጥናት ውስጥ የተሳተፉ የሴት ልጅ ግርዛት የተፈፀመባቸው ልጃገረዶች በሙሉ ለደረጃ [3]/የብልት መሰፋት የግርዛት ዓይነት ተዳርገዋል፡፡ ከአይነታዊ ጥናት ግኝቶቻችንና ከባለድርሻ አካላት ውይይት ቁልፍ ግኝቶች አንዱ አለመገረዝ /ብልትን አለመቆረጥ ሴት ልጅን ባል እንዳታገባ የሚከለክል መሆኑ ነው፡፡ ያላገቡ ወንዶች ልጆችን ባሳተፈ የቡድን ውይይት ወቅት አንድ ተሳታፊ እንዲህ ብሏል፦

> ወንዶች ልጆች ማግባት የሚፈልጉት የተገረዙች ልጃገረድን ነው፤ በሃይማኖታዊ አመለካከት ምክንያት ያልተገረዙችን ልጃገረድ ማንም አያገባም፡፡ ብልታቸው የተሰፋ ልጃገረዶች

---

3 አራት ዋና ዋና የሴት ልጅ ግርዛት ዓይነቶች/ደረጃዎች አሉ፡፡ ደረጃ 1 (clitoridectomy) የሚባለው የቂንጥርን የተወሰነ ክፍል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድን ያመለክታል፡፡ ደረጃ 2 (excision) የሚባለው የቂንጥርን ክፍል ወይም ሁሉንም እና የብልትን የውስጥ ከንፈር (በሴት ብልት ዙሪያ ያሉትን ከንፈሮች) ትልቁን የብልት የውጪ ከንፈር ጨምሮ ወይም እሱን ሳይጨምር ማስወገድን ያካትታል፡፡ ደረጃ 3 (infibulation) የሚባለው የሴት ብልት ከንፈርን በመቁረጥና በመግጠም ወይም በመስፋት የብልት ቀዳዳን ማጥበብን የሚያመለክት ነው፡፡ ደረጃ 4 የሚባለው ደግሞ የብልትን አካባቢ መውጋት፣ መብሳት፣ መቁረጥ፣ መቧጨር ወይም ማቃጠልን ጨምሮ በሴት ብልት ላይ የሚደረጉ ሌሎች ጎጂ አሰራሮችን ያመለክታል፡፡

ጥሩ ናቸው፤ ወንዶች ይፈልጓቸዋል፤ ብልቷ የተዘጋ ከሆነ የራሷና የቤተሰቧ ክብር እንደተጠበቀ ያምናሉ። የሱና[4] / የተከለከሉ የግርዛት ዓይነቶችን ግን እንቃወማለን።

ባህላዊ የሴት ልጅ ብልት ቆራጮች (የማዋለድ ስራም የሚሰሩ) ሴቶች አሁንም የሴት ልጅ ግርዛት ዋና ፈጻሚዎች ናቸው። በአፋር 89% የሚሆኑት እና በሱማሌ 83% የሚሆኑት ልጃገረዶች በነዚሁ ባህላዊ ቆራጮች ብልታቸውን ተቆርጠዋል። በአፋር ክልል 10% የሚሆኑት ልጃገረዶች እና 15% የሚሆኑት የሶማሌ ልጃገረዶች ብልታቸውን እናታቸው እንደቆረጠቻቸው ተናግረዋል። ይሁንና የዓይነታዊ ጥናታችን እንደሚያመለክተው እናቶች ልጃገረዶችን ሲገረዙ አጥብቀው ይይዛሉ እንጂ ብልታቸውን አይቆርጡም። ልጃገረዶች ለመግለጽ እንደሞከሩት የሴት ልጅ ግርዛት እንዲካሄድ በዋናነት የሚወስኑት እናቶች ሲሆኑ ልጃገረዶች በጤና ባለሙያዎች ጭምር እንዲገረዙ ያመቻቻሉ። በሱማሌ የላንኪርታ ቀበሌ ነዋሪ የሆነች የ13 ዓመት ልጃገረድ ስታብራራ፣ ' የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ ውሳኔ የሚሰጡትና ድርጊቱን የሚያስፈጽሙት እናቶች ናቸው።' ብላለች። ከሴት ልጆቻቸው ምላሽና ከላይ ከተጠቀሱት ማሳሰቢያዎች ጋር በተገናኘ ድርጊቱን ለማስቀጠል ዋናው ምክንያት የባህል መለያ መሆኑ (በአፋር 67%፣ በሱማሌ 52%)፤ ሃይማኖታዊ (በአፋር 19%፣ በሱማሌ 41%)፣ እና የልጃገረዶችን ባህሪ ለመቆጣጠር (10% በሁለቱም ክልሎች) ነው ሲሉ እናቶች ተናግረዋል።

ጥቂት የሚሆኑ እናቶች የሴት ልጅ ግርዛት ጉዳት እንደሚያስከትል ያውቃሉ። በአፋር ክልል ከሚገኙት 42% እና በሶማሌ ክልል ከሚገኙት 36% የሚሆኑት ብቻ ድርጊቱ ጉዳት ያስከትላል ብለዋል። የልማዳዊ ድርጊቶቹ የጉዳታቸው መጠን ቢለያይም የሚያስከትሉት የጉዳት ዓይነት በሁለቱም ክልሎች ተመሳሳይ ነው። በአፋር ያሉ እናቶች ትኩረት የሰጡት በምጥ ወቅት መቸገር (95%)፣ በወሲብ ወቅት የሚሰማ ሕመም (50%)፣ እና በሽታ የሚያጋጥም መሆኑን ነው። በሶማሌ ክልል ያሉት ደግሞ ኢንፌክሽን (95%)፣ በምጥ ወቅት መቸገር (53%)፣ በወሲብ ወቅት የሚሰማ ሕመም (33%) ላይ ያተኩራሉ። ስለ ጉዳቱ ማወቅ የሴት ልጅ ግርዛትን ከመቀነስ ይልቅ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ግርዛቱን በህክምና እንዲታገዝ እያደረገ ነው (ሳጥን 2ን ይመልከቱ)። በተጨማሪም፣ በተለይም በሶማሌ (68%) ከአፋር (45%) ጋር ሲነጻጸር የሴት ልጅ ግርዛት ጥቅሞች እንዳሉትም እናቶች ገልጸዋል። የተገለጹት ጥቅማጥቅሞች ልጃገረዶች ጥሩ ባህሪ እንዲኖራቸው (በአፋር 79% እና 91% በሱማሌ) እና ጥሩ ባል እንዲያገኙ (በአፋር 50%፣ በሱማሌ 37%) ይረዳቸዋል የሚሉትን ያካትታል።

ምንም እንኳን የሴት ልጅ ግርዛት እድሜ ልክ አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል ብንገነዘብም (ሣጥን 3 ይመልከቱ)፣ በአንጻራዊ ሁኔታ ጥቂት ልጃገረዶች ብቻ የሴት ልጅ ግርዛት አደጋ እንደሚያስከትል ተናግረዋል። በአፋር ክልል ሴት ልጆች ገና በጨቅላነታቸው የሚቆረጡ እንደመሆናቸው የሴት ልጅ ግርዛት ጉዳት እንዳለው የገለጹት 6% የሚሆኑት ብቻ ናቸው። በሶማሌ ክልል ግርዛት ጉዳት እንደሚያስከትል የተናገሩት ልጃገረዶች 22% የሚሆኑት ናቸው። በተጨማሪም፣ ልጃገረዶች ልክ እንደ እንደእናቶቻቸው ከአደጋው ይልቅ የበለጠ የግርዛትን ጥቅሞች ይገልጻሉ። በአፋር ክልል 23 በመቶ የሚሆኑት ልጃገረዶች፣ በሶማሌ ክልል ደግሞ ከግማሽ በላይ (55%) የሚሆኑት ልጃገረዶች የሴት ልጅ ግርዛት ጥቅም እንዳለው ተናግረዋል። ልጃገረዶች በዋነኛነት የሴት ልጅ ግርዛት በልጃገረዶች መልካም ስነምግባር (በአፋር 89% እና በሶማሌ 84%) እንዲሁም ጥሩ ባል ለማግኘት (በአፋር 28%፣ በሶማሌ 27%) ያለውን ጠቀሜታ ይጠቅሳሉ።

## ሳጥን 2: የሴት ልጅ ግርዛትን በህክምና የማገዝ አዝማሚያ እያደገ ነው።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በ2017 የህክምና ባለሙያዎች የሴት ልጅ ግርዛትን እንዳይፈጽሙ ቢያግድም ድርጊቱ በህክምና የሚታገዝ ከሆነ ማስቀረት ስለማይቻል፣ በተለይ በሶማሌ ክልል የሴት ልጅ ግርዛት በህክምና እየታገዘ መሆኑን ጥናታችን አረጋግጧል። አንዳንድ ምላሽ ሰጪዎች በጤና ጣቢያዎችና በግል ክሊኒኮች ብልት የመቁረጥ ሂደት እየጨመረ መምጣቱን ይናገራሉ። ለምሳሌ በሶማሌ ክልል በሃርሸን ወረዳ ከሚገኙ ማህበረሰቦች መካከል የቀበሌው ሊቀመንበር ይህን ብለዋል።

> ቀደም ባሉት ጊዜያት የሴት ልጅ ግርዛትን በድብቅ እንዲፈጽሙ ይገደዱ ነበር፤ አሁን ግን በአደባባይ በጤና ጣቢያ ያደርጉታል። የማህበረሰብ ጤና ባለሙያዎች ሳይቀሩ የሱና (ደረጃ 1) የግርዛት ዓይነት መፈጸም ኃላፊነቱን ይውስዳሉ። የባህላዊ ገራዦች /የሴት ልጅ ብልት ቆራጮች ሴቶች ሳይቀሩ ስለ ሱና [ደረጃ 1]አስፈላጊነት እና ከደረጃ 1 ውጪ የሆነ የግርዛት ዓይነት በልጃገረዶች ህይወት ላይ ስለሚያመጣው አደጋ መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ሥልጠና እየተሰጣቸው ነው።

በሱማሌ ክልል በላንኪርታ ቀበሌ በቡድን ውይይት ላይ የነበሩ አንድ አባት በተመሳሳይ ሁኔታ ድርጊቱን በመፈፀም ላይ የጤና አጠባበቅ ባለሙያዎች እየተሳተፉ መሆናቸውን እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦

> ከዚህ ቀደም ወንዶች ልጆች ሳይቀሩ እንዲገረዙ ወደ ጫካ ይወሰዱ ነበር፣ አሁን ግን ልጃገረዶችና ወንዶች ልጆች ወደ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ተወስደው እንዲገረዙ እየተደረገ ነው... ድርጊቱን የሚፈጽሙትም በጤና ጣቢያዎች ውስጥ የሚሰሩ ሴት ዶክተሮች ናቸው። የሚያዋልዱት እነሱ ናቸው፤ በግርዛቱ ላይ ላይሳተፉ እንዴት ይችላሉ?

በተጨማሪም አንዳንድ ምላሽ ሰጪዎች እንደገለጹት የግል ፋርማሲዎች ለባህላዊ ብልት ቆራጮች የህመም ማስታገሻ መድሃኒቶችን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ በድብቅ ስልጠና እየሰጡ መሆኑንና ነርሶች እና አዋላጆች አንዳንድ ጊዜ የሴት ልጅ ግርዛትን ለመፈጸም ወደ ልጃገረዶቹ ቤት ጎራ ይላሉ።

* የወንድ ልጅ ግርዛት የጤና ጥቅም እንዳለው እናውቃለን፤ የሴት ልጅ ግርዛት ግን ጉዳት ብቻ ያለው ስልሆነ ድርጊቱን ልናወግዝ ይገባል። ብዙ ኢትዮጵያውያን ግርዛት የሚለውን ቃል ለወንድም ለሴትም ይጠቀሙበታል።

---

4 ሱና ማለት የተከለከለ ማለት ሲሆን ደረጃ 1 የሴት ልጅ ብልት መቁረጥን /ግርዛትን ያመለክታል።

## ሳጥን 3፡ በሴት ልጅ ግርዛት ምክንያት የሚደርስ የህይወት ዘመን የአካልና የስነልቦና ጉዳት

የአይነታዊ ጥናታችን እንደሚያረጋግጠው የሴት ልጅ ግርዛት ለልጃገረዶችና ለሴቶች አንድ ጊዜ ብቻ የሚከሰት የህመም ገጠመኝ ሳይሆን የህይወት ዘመን የጤና እክልና ስቃይ ያስከትላል፡፡ ብልታቸው የተሰፋ ልጃገረዶች ሽንት በሚሸኑበትና በወር አበባቸው ወቅት እንደሚሰቃዩ ገልጸዋል፡፡ ብዙዎች የመሽናት ፍላጎትን ለመቀነስና ተደጋጋሚ የሽንት ቧንቧ ኢንፌክሽን ለመቀነስ ሲሉ ውሃ እንደማይጠጡ ተናግረዋል፡፡

ያገቡ ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሲያደርጉ ተሰፍቶ የነበረው ብልታቸው እንደገና ሲከፈት ሌላው የስቃይ ምንጭ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል፡፡ በሶማሌ ክልል የተሰፋውን ለመክፈት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጤና ባለሙያዎች የሚሳተፉ ቢሆንም፣ ብዙ ጊዜ በባህላዊ ቆራጮች ይከናወናል፡፡ ይህ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህመምን ለመቀነስ ማደንዘዣን እንዲጠቀሙ ባህላዊ ቆራጮችና የጤና አጠባበቅ ባለሙያዎችን በማሰልጠን የተፈጠረ ያልተፈለገ ውጤት እንደሆነ ተገልጿል፡፡ የተሰፋው ብልታቸው እንደተከፈተ ልጃገረዶቹ ወዲያውኑ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አለባቸው፡፡ በአፋር ክልል ባሎች ሚስቶቻቸውን ብልት ለመክፈት ኃይል መጠቀማቸው የተለመደ መሆኑን፣ ጓደኞቻቸው እንደሚያዩላቸው፣ ድርጊቱ ለወንዶችም ጭምር እንደሚያሳምም ይናገራሉ፡፡ በቡድን ውይይት ወቅት በዕድሜው ተለቅ ያል ልጅ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡-

> ልጃገረዶች ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በሚፈጸሙበት ወቅት ወንዱ ድንግልናዋን ለመገሰስ ሲታገል ከባድ ህመም ያጋጥማቸዋል… አዲስ ሙሽሮችም የልጃገረዶችን ድንግልና ሲገስሱ ቀዳዳው በጣም ጠባብ ስለሆነና ጠባሳው በጣም ጠንካራ ስለሆነ ብዙ ይሰቃያሉ፤ ሙሽሮቹ የልጃገረዶቹን ድንግልናን ለመገሰስ በሚታገሉበት ወቅት በሚደርስባቸው ህመም ምክንያት ለሶስት ወይም ለአራት ቀናት ያህል ያነክሳሉ፡፡

በአፋር ክልል አንዳንድ ባሎች ‘ጥንካሬያቸውን’ ለማሻሻልና ትዳራቸውን ለማቆየት ቪያግራ እንደሚወስዱ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ባሎች ጨኸቷን መቋቋም ስለማይችሉ አዲሷን ሚስታቸውን በጓደኞቻቸው እንደሚያስደፍሩ፤ አንዳንድ ባሎች ደግሞ የተሰፋውን ለመቅደድ ቢላዎችን እንደሚጠቀሙና ይህም ለደም መፍሰስና አልፎ ተርፎም ለሞት እንደሚዳርጋቸው ተገልጿል፡፡

ብልታቸውን የተሰፉ ልጃገረዶችና ሴቶች በወሊድ ጊዜ የስነልቦና ጉዳት ያጋጥማቸዋል፤ ለፌስቱላና ለሞት የመጋለጥ እድላቸውም ይጨምራል፡፡ ይህ በተለይ በአፋር ክልል ሴቶች በአራተኛ እርግዝናቸው ወቅት ጠንካራ ጠባሳ ጥሎባቸው እንደሚያልፍ ምላሽ ሰጪዎች ይናገራሉ፡፡

ያደረግናቸው ቃለ መጠይቆች እነዚህን ስሜቶች አረጋግጠዋል፡፡ የ13 ዓመቷ የአፋር ልጅ እንዲህ ስትል ገልጻለች፣ ‘ያልተገረዘች ልጃገረድ ቤተሰቧን ታሳፍራለች… መገረዝ የሚያመጣባት ምንም መጥፎ ነገር የለም፡፡

ለሴት ልጅ ግርዛት ቀጣይነት በአፋር 63% እና በሶማሌ 69% የሚሆኑት እናቶች ጠንካራ ድጋፍ የሚያደርጉ ሲሆን፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ሕገ-ወጥ መሆኑን በአፋር 42% እና በሶማሌ 34% የሚሆኑት እናቶች ግንዛቤው አላቸው፡፡ በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ስለ ህጉ ማወቃቸውን ከሚናገሩት ውስጥ በአፋር ክልል 10 በመቶ፣ በሶማሌ 80 በመቶ የሚሆኑት ደረጃ 1 የግርዛት ዐይነት የተፈቀደ ነው የሚል የተሳሳተ እምነት አላቸው፡፡ እናቶች በዝርዝር ስለተቀመጡት የህግ ቅጣቶች ያላቸው እውቀት ዝቅተኛ ነው፡፡ ወላጆችም ሆኑ ባህላዊ ብልት ቆራጮች ተጠያቂ እንደሆኑ የሚያውቁት ከአምስቱ አንድ (በአፋር 19%፣ በሶማሌ 16%) የሚሆኑት ናቸው ፡፡ ቀሪዎቹ መላሾች (በአፋር 30% እና በሶማሌ10%) በህግ የሚቀጣው ቆራጩ ብቻ ነው ሲሉ፣ ወላጆች ብቻ ይቀጣሉ የሚሉት ደግሞ በአፋር 13% እና በሶማሌ 11% የሚሆኑት ናቸው፡፡

የሴት ልጅ ግርዛት መቀጠል እንዳለበት ከእናቶችና ከታዳጊዎች እምነት ጋር በጣም የተቆራኙትን ምክንያቶች ስንመለከት፣ የትንበያ ትንተናችን (regression analysis) በክልሎች መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት የሚያሳይ ማስረጃ አግኝቷል (ምስል 1ን ይመልከቱ)፡፡ አሁንም ሀይማኖትንና ባህልን ለመለያየት አስቸጋሪ እንደሆነ በማሳሰብ የሴት ልጅ ግርዛት በሃይማኖት የተደነገገ ነው የሚለው እምነት በሁለቱም ክልሎች የድርጊቱ ቁልፍ መነሻ ነው፡፡ ስለ ሴት ልጅ ግርዛት አደገኛነት ግንዛቤ ማስጨበጡ በሁለቱም ክልሎች ድርጊቱ እንዳይቀጥል የሚያደርግ ሲሆን ጥቅም እንደሚሰጥ ማመን ደግሞ በሁለቱም ክልሎች ድርጊቱን ያበረታታል፡፡ ምንም እንኳን የገቢ ልዩነት ማህበራዊ ደንቦችን የመቋቋም ችሎታን እንደሚያሻሽል ቢታመንም በሁለቱም ክልሎች ከእንስሳት እርባታ ወደ እርሻ፣ የደሞዝ ሥራ ወይም የጥቃቅን ንግድ የሚደረግ ለውጥ የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀጠል የእናቶችን ድጋፍ አይቀንሰውም፡፡ እንዲያውም በሶማሌ ክልል እንደዚህ አይነት ለውጥ  የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀጠል የሚየደርጉትን ድጋፍ የሚያሳድገው ይመስላል፡፡

በምስል 1 ላይ እንደተመለከተው፣ የትንበያ ትንተናው የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት ክልላዊ አቀራረቦችን መከተል አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል፡፡ ለምሳሌ የልጃገረዶች የትምህርት እድል በአፋር ክልል ለግርዛት የሚኖረው ድጋፍ አነስተኛ ነው፤ ነገር ግን በሶማሌ ክልል ይህ እንዳልሆነ ተረጋግጧል፡፡ በተመሳሳይ፣ የልጃገረዶች በራስን መተማመን ለሴት ልጅ ግርዛት የሚሰጠው ድጋፍ ከሱማሌ ይልቅ በአፋር ክልል ዝቅተኛ ድጋፍ ጋር የተያያዘ ነው፤ ይህም የህፃናት ጋብቻና በታዳጊነት ዕድሜ እናትነት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከመድረሱ አንጻር ለመጪው ትውልድ ትልቅ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያመላክታል፡፡ በሌላ በኩል የእናቶች ስለ ህግ ያላቸው እውቀት የታየው ከአፋር ይልቅ በሶማሌ ክልል ነው፡፡ የበለጠ ህጋዊ ግንዛቤ ያላቸው የሶማሌ እናቶች ያነሰ ግንዛቤ ካላቸው አኩዮቻቸው ይልቅ የሴት ልጅ ግርዛት እንዲቀጥል የመደገፍ እድላቸው አነስተኛ ነበር፡፡ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ረገድ የክልል ልዩነቶች በተለይ ትኩረት ይስባሉ፡፡ በሶማሌ ክልል የሌለ ግን በአፋር፣ የቤተሰቡን ሀብት የበለጠ የሚቆጣጠሩ እናቶች ከማይቆጣጠሩት ይልቅ ከሶስት እጥፍ በላይ ግርዛትን የመደገፍ እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም ከሶማሌ ክልል ይልቅ በአፋር ልጃገረዶች ዘንድ ከፍተኛ የቤተሰብ ሀብት የሴት ልጅ ግርዛትን እንዲቀጥል ከሚደረግ ድጋፍ ጋር የተያያዘ ነው፡፡

በአጠቃላይ የትንበያ ትንተና ውጤቶቹ እንደሚያሳዩት የሴት ልጅ ግርዛት ስለሚያስከትለው አደጋ የበለጠ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የግርዛት ምርጫዎች ላይ ለውጥ ማድረግና ህግ ማስከበር አስፈላጊ ናቸው። የጥናት ውጤቶቹ አጥብቀው እንደሚጠቁሙት ሴቶችና አባወራዎችን በኢኮኖሚ ማጎልበት ግርዛትን ለማስቀረት የማይረዳ መሆኑን ይልቁንም በተለይም በአፋር ክልል ሴቶች ሀብት የሚያገኙ ከሆነ ለሴት ልጅ ግርዛት ማስፈጸሚያ የሚመድቡ መሆኑን ነው።

## የህፃናት ጋብቻ ሁኔታና አነሳሽ ምክንያቶች

### ቁልፍ ግኝቶች:

- በጥናቱ የተሳተፉት ጥቂት ልጃገረዶች ያገቡ ናቸው። አብዛኞቹ ልጃገረዶች በጣም ትንንሽ ቢሆኑም ግን የህፃናት ጋብቻ በሁለቱም ክልሎች የተለመደ ነው።
- በአፋር ክልል በቤተሰብ የተመቻቸ ጋብቻ የተለመደ ነው። አብዛኞቹ ልጃገረዶች በፈለጉት ጊዜ ማግባት አይችሉም።በአንፃሩ፣ በሶማሌ ክልል አብዛኞቹ ጋብቻዎች የሚፈጸሙት በልጆቹ ጥያቄ ነው።
- ጥቂት የሚሆኑ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ታዳጊዎች ትዳር ለመመሥረት ህጋዊ ዝቅተኛ ዕድሜ እንዳለ የሚያውቁ ሲሆን በሁለቱም ክልሎች አብዛኞቹ ወጣቶች የጋብቻ ተገቢ ዕድሜ ከ18 ዓመት በላይ እንደሆነ ይናገራሉ።
- ልጃገረዶች ከወንዶች ልጆች ይልቅ የህፃናት ጋብቻን ይደግፋሉ።
- የህፃናት ጋብቻ ድጋፍ የሚቀረፀው በማህበረሰብ ደንቦች በመሆኑ የጥናቱ ተሳታፊዎች የተለመደ ነው ብለው በሚያምኑበት ጊዜ የበለጠ ይደግፉታል።
- የእናቶች መማር የህፃናት ጋብቻን ድጋፍ ይቀንሳል።
- በትውልድ መካከል ያለው አንድነት አዋቂዎችና ታዳጊዎች የህፃናት ጋብቻን በሚመለከት ያላቸው እምነት አንዱ የሌላውን ያጠናክራል።
- የትምህርት ተደራሽነት ከሶማሌ ይልቅ በአፋር ክልል የህፃናት ጋብቻ የሚደረገውን ድጋፍ ይቀንሳል።
- በሶማሌ የተሻሉ ቤተሰቦች የህፃናት ጋብቻን የመደገፍ እድላቸው አነስተኛ ነው፤ በአፋር ውስጥ ያለው በተቃራኒው ነው።
- በሶማሌ ክልል በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች በራስ መተማመን የህፃናት ጋብቻን ድጋፍ ይቀንሳል።

በጥናቱ የተሳተፉት ልጃገረዶች አማካይ ዕድሜ 13 የነበረ በመሆኑ፣ በአፋር 3% እና በሱማሌ 4% የሚሆኑት ብቻ ካሁን ቀደም አግብተው የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በአፋር 2% እና በሱማሌ 3% የሚሆኑት ትዳር የያዙና 1% የሚሆኑት ደግሞ አግብተው የፈቱ ናቸው። ከእነዚህ ልጃገረዶች መካከል በጋብቻ ውስጥ ያሉት አማካይ ዕድሜያቸው ተመሳሳይ ነበር (በአፋር 15.8 ዓመት እና በሱማሌ 15.6 ዓመት)። ከአንድ አምስተኛ በላይ (22%) የሚሆኑት በሁለቱም ክልሎች የሚገኙ ልጃገረዶች 15 ዓመት ሳይሞላቸው አግብተዋል። ይሁን እንጂ የጋብቻው ዓይነት በየክልሎቹ በጣም የተለያየ ነው። በአፋር ክልል 87% የሚሆኑት ልጃገረዶች በአብሱማ(የጎሳ አንድነትን ለመጠበቅ የእናት ወንድም ልጅ ጋብቻ) ባህል መሰረት ጋብቻ ፈፅመዋል። ከአንድ ሶስተኛ በላይ (36%) የሚሆኑት በጊዜው ለማግባት ዝግጁ እንደነበሩ ገልጸዋል (ሳጥን 4ን ይመልከቱ)። በአንፃሩ በሶማሌ ክልል 21% የሚሆኑት ብቻ በቤተሰብ ያገቡ ልጃገረዶች ብቻ የተመቻቸ ጋብቻ መፈጸማቸውን ተናግረዋል። በሶማሌ ክልል በጥናቱ የተሳተፉት በጣም ጥቂት ልጃገረዶች ቀደም ብለው ያገቡ ሲሆን ያገቡት ልጃገረዶች ሁሉም ማለት ይቻላል (97%) በአካባቢያቸው ያሉት አማራጮች ውሱን መሆናቸውንና ባገቡበት ሰዓትም ለማግባት ዝግጁ የነበሩ እንደሆኑ ይሰማቸዋል።

በጥናቱ ከተሳተፉት ሴቶች መካከል፣ በሶማሌ 58 በመቶ ጋር ሲነጻጸር  በአፋር 88 በመቶ የሚሆኑት በጣም ብዙዎቹ ሴቶች ከ18 ዓመታቸው በፊት ያገቡ ሲሆን፣ ባገቡበት ወቅት አማካይ ዕድሜያቸው በአፋር 16.2 ዓመት፣ በሶማሌ ደግሞ 17.3 ዓመት ነበር። በሶማሌ 74% ከሚሆነው ጋር ሲነጻጸር፣ በአፋር ክልል ሁሉም ማለት ይቻላል የእናቶች ጋብቻ (97%) በቤተሰብ የተመቻቸ ነበር። ጋብቻ በፈጸሙበት ወቅት ለማግባት ዝግጁ እንደሆኑ በተናገሩት ሴቶች ቁጥር ላይ ከፍተኛ ልዩነት ነበር። ይኸውም፣ ከሶማሌ 77% ጋር ሲነጻጸር በአፋር ክልል ከግማሽ በታች (38%) ነበር።

የህፃናት ጋብቻን ለማስቀጠል ማህበራዊ ደንቦች ትልቅ ሚና ይጫወታሉ። በሁለቱም ክልሎች አብዛኞቹ እናቶች (በአፋር 87%፣በሶማሌ 79%) እና በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች (በአፋር 87%፣ በሶማሌ 54%) ሴት ልጅ 18 ዓመት ሳይሞላት ማግባት የተለመደ እንደሆነ ያምናሉ። ከዚህም በላይ በጣም ጥቂት ታዳጊዎች (በአፋር 7% ፣ በሱማሌ2%) ከ18 አመት በታች ጋብቻ ህገወጥ መሆኑን ተገንዝበዋል። ይህም ሆኖ፣ በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች እንደ ትልቅ ሰው ማግባት እንደሚፈልጉ ተናግረዋል። በአማካይ ለትዳር ተስማሚ የሆነው እድሜ በአፋር 19 አመት እና በሶማሌ 20.7 መሆኑ ተገልጿል። በተጨማሪም በጉርምስና ዕድሜ ላይ ከሚገኙት ወጣቶች መካከል ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት (64%) በአፋር እና ከግማሽ በላይ የሚሆኑት (53%) በሱማሌ ክልል ለጋብቻ ተስማሚው ዕድሜ 18 ዓመትና ከዚያ በላይ እንደሆነ ተናግረዋል። በጉርምስና ዕድሜ ላይ የሚገኙ ወጣቶች እንደገለጹት፣ ልጃገረዶች ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ፣ ለትዳር የበለጠ አካላዊና አእምሮአዊ ዝግጅት እንዲኖራቸው አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምኑ ተናግረዋል።

የህፃናት ጋብቻን ቀጣይነት ድጋፍ ከማድረግ ጋር የተቆራኙትን ምክንያቶች ስንመለከት፣ በአካባቢያዊ ልማዶች ዙሪያ የሚደረጉ የማስተካከያ እርምጃዎች በጥንቃቄ መሰራት እንደሚያስፈልጋቸው የትንበያ ትንተናችን ያሳያል (ምስል 2ን ይመልከቱ)። ለምሳሌ፣ ልክ በሴት ልጅ ግርዛት ላይ እንደሆነው ሁሉ፣ ከሶማሌ ክልል ይልቅ በአፋር ክልል የታዳጊዎች የትምህርት እድል ማግኘት ለህፃናት ጋብቻ አነስተኛ ድጋፍ ጋር ይያያዛል። በተመሳሳይ በአፋር ክልል ብቻ የታዳጊዎች ስለ ጋብቻ ህጋዊ ዕድሜ ያላቸው እውቀትና በባህላዊ ውዝዋዜዎች ላይ መሳተፍ

## ስዕል 1: በሴት ልጅ ግርዛት ዙሪያ የተገኘ የትንበያ ትንተና ውጤት

**በታዳጊዎች** ሞዴል ብቻ
የተካተተና ጉልህ የሆነ


በወላጆች/ አሳዳጊዎች ሞዴል
ብቻ የተካተተና ጉልህ የሆነ

በታዳጊዎች እና በወላጆች/
አሳዳጊዎች ሞዴል የተካተተ - ነገር
ግን **በታዳጊዎች** ብቻ ጉልህ የሆነ



በታዳጊዎች እና በወላጆች/ አሳዳጊዎች
ሞዴል የተካተተ - ነገር ግን በወላጆች/
አሳዳጊዎች ብቻ ጉልህ የሆነ

በታዳጊዎች እና በወላጆች/
አሳዳጊዎች ሞዴል የተካተተና
በሁሉም ጉልህ የሆነ



## ሳጥን 4: በአፋር የህፃናት ጋብቻ ለውጦች

ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶች በአፋር የአብሱማ ጋብቻዎች በሁሉም ቦታ እንደሚገኙ ሲያሳዩ (Jones et al., 2019; Presler-Marshall et al., 2020)፣ የዓይነታዊ ጥናታችን ግኝቶች ምንም እንኳን መጀመሪያ ላይ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የነበሩ ቢሆኑም አንዳንድ ለውጦችን ያሳያሉ። አንዳንድ ወላጆች ስለትዳር በሚደረጉ ውሳኔዎች ላይ ልጃገረዶች የበለጠ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ ዕድል ሲሰጧቸው ይታያሉ። ይህም በዋነኛነት ስል ፍቅረኛሞች ጥቃት/ጠብ ግንዛቤ መጨመርና የፍቺ መጠን እየጨመረ በመምጣቱ ነው። እንደ ቁልፍ መረጃ ሰጪ ቃለ መጥይቅ የተደረገላቸው አንዳንድ የሀይማኖት መሪዎች በቁርዓን ውስጥ አብሱማ ጋብቻን የሚደግፍ ምንም ነገር እንደሌለ አሳይተዋል። በተጨማሪም ልጃገረዶች አብሱማ ጋብቻን በመቃወም እና ሊያጋቧቸው መሆኑን ሲያውቁ በወረዳ ደረጃ ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ለመምህራን፣ ወይም ከተሜ በሆነው የአይሳኢታ ወረዳ ደግሞ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ሪፖርት እንዳደረጉ በርካታ መረጃዎችን አግኝተናል። የኮሮ ዶራ ቀበሌ ነዋሪ የሆነች የ16 አመት ልጃገረድ እንደገለፀችው፡-

> በአሁኑ ጊዜ አብሱማ የጋብቻ ባህል እየቀነሰ ነው… የጋብቻ ሂደቱ ሴት ልጅ ልክ ለአቅመ ሄዋን እንደደረሰች ወላጆቿ ልጃቸውን ሊያገባ የሚችል ወንድ መፈለግ ይጀምራሉ። ሙሽራውና ሙሽሪቷ የመጀመሪያ የአጎት ልጆች ከሆኑ በወላጆች ድጋፍ ይከናወናል። ነገር ግን በተጋቢዎቹ የፍቅር ግንኙነት ከሆነ በራሳቸው ፍላጎት ይከናወናል፤ እዚህ ላይ ወላጆች አብዛኛውን ጊዜ አይሳተፉም።

የአብሱማ ጋብቻ ዓለም አቀፋዊ እንዳልሆነ የሚያሳዩ አንዳንድ ማስረጃዎች ቢኖሩም የሃይማኖት መሪዎች አሁንም የህፃናት ጋብቻን ይደግፋሉ። ልጃገረዶችን በተለይም በ15 ዓመታቸው አካባቢ የመጀመሪያ ወር አበባቸውን ካዩ በኋላ ወዲያው እንዲያገቡ ያበረታታሉ፤ ምክንያቱም ቀደም ብሎ ቶሎ ቶሎ ልጅ መውለድ ለጎሳው ታላቅነት ጠቃሚ ሆኖ ይታያል።

የህፃናት ጋብቻ ድጋፍን እንደሚቀንስ ተረጋግጧል። በሌላ በኩል የታዳጊዎች በራስ መተማመን በሶማሌ ክልል የህፃናት ጋብቻ የሚደረገው ድጋፍ ዝቅተኛ ሲሆን በአፋር ክልል ግን አልነበረም። ከኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አንፃር፣ በክልሎች ያለው ሁኔታ በጣም ተቃራኒ ነው፤ ምናልባት በአፋር ውስጥ ሀብታም አባወራዎች በገጠር የሚኖሩ ሲሆኑ በሶማሌ ክልል ደግሞ የበለጠ ከተማ የመኖር አዝማሚያ ስላላቸው የከተሞች መስፋፋት ለሚያመጣቸው እድሎች ይጋለጣሉ። በሶማሌ ውስጥ ከፍተኛ የቤተሰብ ሀብት (በንብረት መረጃ ጠቋሚ ሲለካ) የህፃናት ጋብቻን የሚከላከል ሆኖ ተገኝቷል። በአፋር የሆነው በተገላቢጦሹ ነው። በተመሳሳይ በአፋር ከከብት እርባታ ወደ ሰብል እርባታ የሚደረግ ለውጥ የህፃናት ጋብቻ ጋር የተያያዙ ድጋፎችን እንደሚቀንስ ሲታወቅ በሶማሌ ክልል ግን ከፍተኛ ድጋፍ የሚያስገኝ መሆኑ ተገልጿል። ከከብት እርባታ ወደ ጥቃቅን ንግድ የሚደረግ ሽግግር በሶማሌ ክልል ለልጃገረዶች የህፃናት ጋብቻን የሚከላከል ሆኖ ተገኝቷል። በአፋር የሆነው ግን የተገላቢጦሽ ነበር።


## መደምደሚያ

የኢትዮጵያ መንግስትና የልማት አጋሮቹ የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን ለማስቀረት ባላቸው ቁርጠኝነት ላይ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት መሰራት ያለበት ገና ብዙ የሚቀረው ስራ እንዳለ ጥናታችን አጉልቶ ያሳያል። በእርግጥም ጥናት ባካሄድንባቸው የአፋርና የሶማሌ ማህበረሰቦች የሴት ልጅ ግርዛት ተፈላጊነቱ እየቀነሰ መምጣቱን፣ የተለመደ አለመሆኑን፣ እንዲሁም ብልት መስፋት በሌሎች ቀለል ባሉ የግርዛት ዓይነቶች የተተካ መሆኑን የሚያሳይ ምንም አይነት መረጃ አላገኘንም። እንዲያውም በሕክምና እየታገዘ የሚከናወን መሆኑን የሚያሳዩ አንዳንድ ማስረጃዎችን አግኝተናል። ከዚህም በላይ በሶማሌ ክልል የህፃናት ጋብቻ በጣም እየተለመደ መምጣቱንና ልጃገረዶች የሚያገቡበት ዕድሜ እየቀነሰ መሄዱን ጥናታችን ያመለክታል። እነዚህ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ልጃገረዶችና ሴቶችን ልጅ የመውለድ አቅማቸውን ብቻ ዋጋ በሚሰጡ እና የትምህርት እድልን፣ የስራና፣ ውሳኔ ሰጪነትን በሚገድቡ የስርዓተ-ፆታ ደንቦች የተጠናከሩ ናቸው። የአፋር እና የሶማሌ ክልል መንግስታት ግርዛትም ሆነ የህፃናት ጋብቻ ህገወጥ ናቸው የሚለውን የኢትዮጵያ ቤተሰብ ህግ አላጸድቅም ማለታቸው ለድርጊቱ ቀጣይነት አስተዋጽኦ አድርጓል።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ምርምራችን አንዳንድ የለውጥና የተስፋ ጭላንጭሎችንም አግኝቷል። የሴት ልጅ ግርዛትን በተመለከተ፣ ጎልማሶች ድርጊቱን የሚከለክሉትን ሀገራዊ ህጎች ቀስ በቀስ እየተገነዘቡ፣ የሃይማኖት መሪዎችም የብልት መስፋትንና የቂንጥር መቁረጥን አደገኛነት እያወቁ መጥተዋል። የህፃናት ጋብቻን በተመለከተ በአፋርም ሆነ በሶማሌ ያሉ ልጃገረዶች በወላጆቻቸው ከተመረጠላቸው ይልቅ ራሳቸው የፈለጉትን የትዳር አጋር ማግባት መቻላቸው እንዲሁም ታዳጊዎች ከ18 ዓመታቸው በኋላ ማግባት ፍላጎታቸው እየጨመረ መጥቷል።

ለወደፊት እድገት ወሳኝ የሆነው፣ የሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ እንዲቀር ከተፈለገ በክልሎች የድርጊቱ መመሳሰልና ልዩነቶች ላይ ማተኮር አስፈላጊ መሆኑን ጥናታችን አጉልቶ ያሳያል። ይኸውም፣ በሁለቱ ክልሎች የሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዴት እንደሚመሳሰሉና እንደሚለያዩ እንዲሁም በየክልሎቹ በሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ አነሳሽ ምክንያቶች መካከል ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት ያጠቃልላል። ለምሳሌ፣ ጥናታችን ምንም እንኳን የሴት ልጅ ግርዛት (እንዲሁም ብልት መስፋት) በአፋርም ሆነ በሶማሌ ክልል በተለመደው ሁኔታ እንደሚቀጥል ቢያረጋግጥም ስለሚያስከትለው ጉዳት፣ አለው ተብሎ ስለሚታሰበው ጥቅም፣ እና ስለ ህጉ የግንዛቤ ማስጨበጫ በሁለቱም ክልሎች ልማዳዊ ድርጊቱን ለመቀነስ ወሳኝ መሆኑን የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራውም በአግባቡ መከናወን እንዳለበት ይጠቁማል። ይህም ልጃገረዶች የሚገረዙበት እድሜ (በአፋር ጨቅላነትና በሱማሌ በልጅነት ዕድሜያቸው መጨረሻ ላይ) እና ትምህርት ከሶማሌ ክልል ይልቅ በአፋር የሴት ልጅ ግርዛት ድጋፍን የሚቀንስ መሆኑን ያካትታል። በተጨማሪም የሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ ሁለቱም የሴት ልጅ ዋጋ በትዳርና በእናትነት ላይ ብቻ የተገደበ ነው የሚለውን ስር የሰደደ እምነት የሚያንፀባርቁ በአንዳንድ መልኩ የአንድ ሳንቲም ሁለት

# ስዕል 2: በህጻናት ጋብቻ ዙሪያ የተገኘ የትንበያ ትንተና ውጤት



ገፅታዎች ቢሆኑም ልማዳዊ ድርጊቶቹን ለማስቀረት መንገዶቹ በአብዛኛው የተለያዩ መሆናቸውንና ካለዕድሜ ጋብቻ ይልቅ የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቀረት በጣም ከባድ ሊሆን እንደሚችል ጥናታችን አመልክቷል፡፡ በእርግጥም ምንም እንኳን ሴቶችንና ቤተሰባቸውን በኢኮኖሚ ማጎልበት የሴቶች ልጆችን የህፃናት ጋብቻ ስጋት ቢቀንስም የሴት ልጅ ግርዛትን ግን የበለጠ ሥር መስደድን ሊያስከትል የሚችል ይመስላል፡፡

## የፖሊሲና ፕሮግራም አንድምታ

ምንም እንኳን ወደፊት በሌላ ዙር የሚደረጉ ጥናቶች ለውጥ ለማምጣት ውጤታማ መንገዶችን በተመለከተ የበለጠ ግንዛቤን የሚሰጡ ቢሆንም የኢትዮጵያ መንግስትና የልማት አጋሮቹ የህፃናት ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም በተዘጋጀው የሀገር አቀፍ ፍኖተ ካርታ ላይ እድገትን ለማፋጠንና የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ከፈለጉ በትልቁ ማሰብ እንዳለባቸው የመሠረታዊ የጥናት ግኝታችን ይጠቁማል፡፡ የሚደረጉ ጥረቶች በሚገባው ልክ ከሆኑ፣ በየሴክተር ዕቅዶች ከተካተቱ፣ በየሴክተሮችና የመንግስት እርከኖች እንዲቀናጁ ከተደረገ፣ በህጻናትና በሥርዓተ-ፆታ ላይ ካተኮሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እውቀት የተወሰዱ ከሆነ፣ ከባህላዊ እና ከሃይማኖት መሪዎች ጋር በመነጋገርና ሁሉንም የማህበረሰብ አባላት - ጎልማሶች፣ ሴቶችና ወንዶችን፣ ልጃገረዶችና ወንዶችን -ያሳተፉ ከሆነ የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን ለማስቀረት የሚጫወቱት ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ የሚከተሉትን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን እርምጃዎች እንጠቁማለን፡፡

## የሕጉን ግንዛቤ ማሳደግና የተላለፉትን ለህግ ማቅረብ

የአገራዊ ህግ እውቀትና አፈፃፀም ውስን ነው ተብሎ ስለተገለጸ የፍትህ ሴክተሩ በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ አገራዊ ህጎችን የማስተዋወቅና የማስከበር ጥረቱን እንዲያጠናክር እናሳስባለን፡፡ ይህም የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡፡

- ማንኛውም አይነት የሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ ህገወጥ መሆናቸውን ማህበረሰቡ እንዲያውቅ ከባህላዊና ከማህበረሰብ መሪዎች ጋር መስራት፤
- የልጃገረዶችና የሴቶችን የመማር፣ ውርስ የማግኘት፣ እና ከጥቃት ነጻ የመሆን መብታቸውን ለማሻሻል ከሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ጋር መስራት እንዲሁም በሸሪዓ ፍርድ ቤቶችና በመደበኛ ፍርድ ቤቶች የፍትህ ስርዓት መካከል ያለውን ትብብር ማሳደግ፤
- የታቀዱ የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን ለመከላከል የሚያስችሉ ማንነትን የማያሳውቁ የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን (ምናልባትም በትምህርት ቤት) ማቋቋም፤
- ለሚፈጸሙ ጥቃቶች ተፈጻሚ የሚሆኑ ቅጣቶችን በቀበሌ ደረጃ ለማወጅና የቁጥጥር ዘዴዎችን ለማጠናከር ከማህበረሰቡ ጋር በመስራት፤
- መብቶቻቸውን የበለጠ እንዲያውቁና እንዴት እንደሚጠይቁ ለማሳወቅ ከልጃገረዶችና ሴቶች ጋር በመስራት፤
- ህጉንና የመተላለፍ ቅጣቶችን የበለጠ እንዲያውቁ ከወንዶች ልጆችና ከአዋቂ ወንዶች ጋር በመስራት፤
- የክልል ህጎች የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን ከሚከለክሉ ብሄራዊ ህጎች ጋር እንዲጣጣሙ ከክልል



ከጋብቻ በፊት ወደ ዩኒቨርሲቲ መግባትና ስራ መያዝን መመኘት፡ የ15 አመት ልጅ ከአፋር © ናታሊ በርትራምስ / ጌጅ 2014 ዓ. ም.

መንግስታት ጋር መመካከርና የቤተሰብ ህጉን በማፅደቅ እነዚህ ድርጊቶች በወንጀል እንዲጠየቁ ማድረግ፤

## የልጃገረዶችንና የሴቶችን ህይወት እና የህይወት ምርጫ የሚገድቡ የስርዓተ-ፆታ ደንቦችንና ልምዶችን ለመቀየር ከልጃገረዶችና ሴቶች ጋር መስራት

የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን የሚያበረታቱ ተመሳሳይ የስርዓተ-ፆታ ደንቦች የልጃገረዶችና ሴቶች ትምህርትና ሥራ እንዳያገኙ እንዲሁም በውሳኔ አሰጣጥ ላይ አስተያየት እንዳይሰጡ ስለሚከለክሏቸው የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ እነዚህን እምነቶችና ድርጊቶች በቀጥታ እንዲያስቆም እናሳስባለን። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ሴቶች ስለራሳቸው (እና ሴት ልጆቻቸው) መብት እንዲያውቁና ጥቃቶችን እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርጉ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ጥረት ማድረግ።
- ሴቶች (እና ልጃገረዶች) የተነፈጉትን መደበኛ ትምህርት የማግኘት፣ ማንበብና መፃፍ እና የቁጥር እውቀትን ጨምሮ ልዩ ልዩ ክህሎት የሚያዳብሩበት መንገዶችንና እድሎችን መፍጠር፤
- እናቶች ሴቶች ልጆቻቸውን አቅም እንዲያጎለብቱና ወንዶች ልጆቻቸው ያልተገረዙ ልጃገረዶችን 'እንዳያገቡ' ከሚከለክሉ ደንቦች መራቅን ጨምሮ አማራጭ ባህርያትን እንዲከተሉ ለማበረታታት ከእናቶች ጋር መስራት፤
- ስለ ልጃገረዶች ትምህርት አስፈላጊነትና እንዴት በተግባራዊ ሁኔታ መደገፍ እንደሚቻል ግንዛቤ ለማስጨበጥ ከማህበረሰቡ ጋር መስራት፤
- የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን በሚመለከት ባለው ክልላዊ ተጨባጭ ሁኔታ ውሳኔ ሰጪነትና ተጠያቂነትን ማስፈን፤ ልጃገረዶችንና ቤተሰቦችን እንዲሁም ማህበረሰቦችን ስለነዚህ ልማዳዊ ድርጊቶች ጉዳት በማስተማር፤ ትክክለኛውን ግንዛቤ ማሳደግ፤
- ወሲባዊና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች ለደረሰባቸው አገልግሎቶችን (የማገገሚያ ማዕከላትን ጨምሮ) ማጠናከር፤
- የተገረዙ/ ብልታቸውን የተቆረጡ ልጃገረዶች በተለያዩ የሕይወት ዘመናቸው ተገቢውን የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ከጤና ቢሮዎች ጋር በመስራት፤

## የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ግንዛቤ ለማስጨበጥና አማራጭ ባህርያትን ለማበረታታት ከአዋቂ ወንዶችና ከወንዶች ልጆች ጋር መስራት

አባቶች፣ ወንድሞች፣ ወንድ ጓደኞች፣ ወንድ የዕድሜ አቻዎች፣ እና ባሎች የሴት ልጅ ግርዛትን ጨምሮ ልጃገረዶችንና ሴቶችን የሚጎዳውን ሰፋ ያለ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች ለማስቀጠል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያደርጉ በመሆናቸው፣ የወንድ አመለካከትን እና ልምዶችን ለመቀየር መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት በተብብር መሥራት አለባቸው። ይህም የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል።

- አባቶችና ወንድሞች ሚስቶቻቸውንና እህቶቻቸውን ልጃገረዶች ትምህርታቸውን ለማጥናት ነጻ እንዲያደጓቸው እንዴት በተሻለ ሁኔታ መደገፍ እንደሚችሉ እንዲገነዘቡ መርዳት፤
- የተገረዘችን ሴት ማግባት ለምን አስፈላጊ እንዳልሆነ እና ወንዶች ልጆችና አዋቂ ወንዶች እህቶቻቸውንና ሴት ልጆቻቸውን እንዴት እንደሚከላከሉ እንዲሁም በሚስቶቻቸው ላይ ተጨማሪ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ማስተማር፤
- በማህበረሰቡ ውስጥ የወንዶችን ከሴት ልጆች የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ንፅህናና 'የተሳካ' ጋብቻ ጋር በተያያዘ ካለባቸው የተዛባ አመለካከት ለማላቀቅ መሥራት፤
- ወንዶችን ልጆችንና አዋቂ ወንዶችን ዕድሜዋ ለጋብቻ የደረሰች ሚስት ማግባት ያሉትን ተግባራዊ ጥቅሞች እና የህፃናት ጋብቻ/ ዕድሜዋ ለጋብቻ ያልደረሰ ልጅ ማግባት የሚያስከትለው ጉዳት ማስተማር፤
- አባቶች ልጆቻቸውን በተለየ መንገድ ማሳደግ የሚችሉት እንዴት እንደሆነ ጨምሮ የበለጠ ፍትሃዊ የቤተሰብ ውሳኔ መስጠትን እና ጉልበት ያልታከለበት ግንኙነትን ማበረታታት፤

## በሰፊው ማህበረሰብ ውስጥ የልጃገረዶችንና የሴቶችን ህይወት የሚገድቡ የስርዓተ-ፆታ ደንቦችንና ልምዶችን ለመቀየር ከአዋቂዎችና ታዳጊዎች ጋር መስራት

የሴቶችንና የልጃገረዶችን ሕይወት የሚገድበው የሥርዓተ-ፆታ ደንቦች ሌሎች የማኅበረሰብ አባላትና መሪዎች እነዚህን ደንቦች የመለየትና የመፍትሄ ሃሳቦችን የመስጠት አቅም ስለሚገድቡ፣ በሕጻናትና ስርዓተ-ጾታ ላይ አተኩረው የሚሰሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከታዳጊዎችና ጎልማሶች ጋር በመተባበር እነዚህን እምነቶችንና ልምዶችን መቀየር እንዲሁም የአካባቢውን አቅም ማጎልበት አለባቸው። የሚወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎችና ውጤታቸው ባግባቡ መመዘን የሚኖርባቸው ሲሆን የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው።

- ልጃገረዶች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙና በትምህርታቸው የላቀ ደረጃ እንዲደርሱ መደገፍ፤
- ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቀየር ወይም የትውልድ ለውጥ ለማማምጣት ታዳጊዎችን በሴት ልጅ ግርዛት እና የህፃናት ጋብቻ ጉዳዮች ላይ ማሳተፍ፤
- ሴቶች ስለራሳቸውና ሴት ልጆቻቸው መብት እንዲማሩ እና መብታቸውን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ እንዲያውቁ መደገፍ፤
- የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችና በልጃገረዶችንና ሴቶች ላይ ስለሚያደርሱት ጉዳት ለእናቶች እና ለአባቶች ትምህርት መስጠት፤
- በትምህርት ቤቶች የሚቋቋሙ የልጃገረዶችና የሥርዓተ-ፆታ ክለቦችን ማጠናከር፤
- አርአያ የሚሆኑ ሰዎችን መደገፍና ከአካባቢው አመራሮች እና አገልግሎት ሰጪዎች ጋር በመሆን የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህፃናት ጋብቻ አደጋዎችን ግንዛቤ ማስጨበጥ፤

## እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መጨረሻ ድረስ ሁሉም ልጃገረዶች የትምህርት እድል ማግኘት መቻላቸውን ማረጋገጥ

ሴቶች ከወንዶች ይልቅ ከትምህርት የመገለል እድላቸው ከፍተኛ በመሆኑ የትምህርት ሴክተሩ ቢያንስ እስከመካከለኛ ደረጃና እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ድረስ ሁሉም ልጃገረዶች የትምህርት እድል እንዲያገኙ የሚያደርገውን ጥረት እጥፍ እንዲያደርግ እናሳስባለን። ይህም የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል።

- ሁሉም ማህበረሰቦች (ዘላኖች አርብቶ አደሮችን ጨምሮ) ቀደም ሲል የትምህርት እድል ለተነፈጉ ትልልቅ ልጃገረዶችና ሴቶች የጎልማሶች ትምህርትን ጨምሮ ቢያንስ እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጥራት ያለው ትምህርት የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች መኖራቸውን ማረጋገጥ፤
- ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት በማይልኩ ወላጆች ላይ ተገቢውን ቅጣት ማድረግን ያካተተ ከትምህርት ውጪ የሆኑትን ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ለማስገባት የቤት ለቤት ቅስቀሳ ማድረግ፤
- ወሲባዊና ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃትን ጨምሮ በሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ ላይ ያተኮረ ተጓዳኝ ስርዓተ-ትምህርትን ማስፋፋት፤
- ከድሃ ቤተሰብ ለመጡ ተማሪዎች የትምህርት ቤት ቁሳቁስ አቅርቦቶች ማሟላት፤
- በትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብሮች፣ በትምህርት ቤት የንፅህና መጠበቂያ እና የወር አበባ ንፅህና መጠበቂያ አቅርቦቶች፣ አሳታፊ የልጃገረዶች/የሥርዓተ-ፆታ ክለቦች፣ እና የማጠናከሪያ ስልጠናዎች ላይ ኢንቨስትመንቶችን ማጠናከር፤
- በመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላሉ ተማሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ተመጣጣኝ የአዳሪ ትምህርት ቤት አማራጮችን መጠቀም፤
- በወረዳ ደረጃ ትምህርት ጽ/ቤቶች ደረጃ በቂ ክትትል ማድረግ፣ የመምህራንን ከስራ መልቀቅንና መቅረትን ለመቀነስ እንደ አስፈላጊነቱ ለመምህራን ማበረታቻዎችን መጠቀም፤

## ትምህርትን ለማበረታታትና የህፃናት ጋብቻን ለማዘግየት ማህበራዊ ጥበቃን መጠቀም

አለም አቀፋዊ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የህፃናት ጋብቻን ለመከላከል ከሁሉ የተሻለው መንገድ ልጃገረዶችን በተቻለ መጠን ለረጅም ጊዜ በትምህርት ቤት ማቆየት በመሆኑ ወላጆች ልጃገረዶችን እንዲያስተምሩ ለማበረታታት እና ጋብቻን ለማዘግየት ማህበራዊ ጥበቃን በመጠቀም ያስፈልጋል። ይህም የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል።

- ለልጃገረዶች ተጨማሪ ለቤት ከሚወስዱት ራሽን ጋር የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብሮችን መጀመር/ማስቀጠል፣
- ልጃገረዶችና ሴቶች የራሳቸውን ገቢ ማግኘት እንዲችሉ የንብረት ማስተላለፍ፤
- መገለልን እና መድሎን ለመቋቋም፣ እነዚህን ጎጂ ልማዶች በንቃት ለሚቃወሙ ቤተሰቦች የህግ ድጋፍ እና ማህበራዊ ጥበቃ ማድረግ አንዱ አማራጭ ነው። እነዚህ ቤተሰቦች ለሌሎች አርአያ ሊሆኑ ይችላሉ።

## የመተዳደሪያ አማራጮቻቸውን ለማሻሻል ከሴቶችና ልጃገረዶች ጋር መስራት

ልጃገረዶችና ሴቶች የራሳቸውን ገቢ ለማግኘት ያሏቸው እድሎች በጣም ጥቂት ስለሆኑ የግብርናና የስራተኛ ሴክተር የሴቶችን የመተዳደሪያ አማራጮችን የማስፋት ጥረቶችን ማጠናከር ይኖርበታል። እነዚህም ከገንዛቤ ማስጨበጫ ጋር ተጣምረው ልጃገረዶችና ሴቶች የተሻሻለ የፋይናንስ ተደራሽነት የሴት ልጅ ግርዛትን እንዳያስፋፋ እርግጠኛ መሆንና የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል።

- የልጃገረዶችንና የሴቶችን የመደበኛ ትምህርት ተደራሽነት ውስንነት ለማካካስ ማህበረሰብ-ተኮር የሴቶች ብቻ የማንበብና መጻፍ እና መሰረታዊ የቁጥር ትምህርት መስጠት፤
- የእንስሳት እርባታ እና ሌሎች በባህላዊ ተቀባይነት ያላቸውን የሙያ ክህሎቶችን ጨምሮ ለትላልቅ ልጃገረዶች እና ሴቶች ከህይወት ክህሎቶች እና የገንዘብ / የንግድ ክህሎቶች ጎን ለጎን ስልጠና መስጠት፤
- ለትላልቅ ልጃገረዶችና ሴቶች መደበኛ የቁጠባ እና የብድር ተቋማትን የሚያገኙበትን ተጨማሪ እድሎች መፍጠር።

## ለልጃገረዶችና ሴቶች ማህበራዊና ህጋዊ ለውጦችን ከፍ ለማድረግ በአፋርና በሶማሌ ክልሎች በሚገኙ የክልሉ መንግስት አመራሮች

የአፋር እና ሶማሌ ክልሎች በሌሎች ክልሎች የታዩትን እድገት ገና እያረጋገጡ ባለመሆናቸው፣ የክልሎቹ የመንግስት አመራሮች የልጃገረዶችን እና የሴቶችን ህይወት የሚያሻሽሉ ማህበራዊ እና ህጋዊ ለውጦችን እንዲያራምዱ እንጠይቃለን። እነዚህም ተግባራት:

- ለውጥን እንዲመጣ ፈቃደኛ የሆኑ ሻምፒዮናዎችን (በተለይ የጎሳና የሃይማኖት መሪዎችን) ለመለየት ጥረት ማድረግ፤
- የክልል ሕጎችን ከብሔራዊ ሕግ ጋር ለማስማማት ጥምረት መፍጠር፤
- ልጃገረዶችና ሴቶች መብቶቻቸውን እንዳይጠቀሙ የሚከለክሉትን የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችንና ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመቋቋም በቂ የሰው እና የገንዘብ ሀብቶችን መመደብ፤
- የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻ ስርጭቱ ከፍተኛ በሆነባቸው ሩቅ አካባቢዎች ላይ በማተኮር ችግሩን ለመቅረፍ የተነደፉ ፕሮግራሞችን በማስረጃ ላይ በተመሰረተ ክትትልና ግምገማ ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤

## ሰዎች ጎጂ ልማዶችን እንዲተዉና ወሲባዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን የሚደግፉ የስርዓተ-ፆታ ደንቦችን እንዲቀይሩ የሃይማኖት መሪዎችን ማሳተፍ

የሴት ልጅ ግርዛት እንደ ሀይማኖታዊ ግዴታ ስለሚታይ እና የህፃናት ጋብቻም ሃይማኖታዊ ተቀባይነት ያለው በመሆኑና

ተመራጭ ነው ተብሎ የሚታመንበት በመሆኑ ሁሉም ተዋናዮች (መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ) እነዚህን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ለማስቀረት ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ተቀራርበው መሥራት አስፈላጊ ነው። ይህም የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል።

- የሀይማኖት አባቶች የሴት ልጅ ግርዛትን እና የህፃናት ጋብቻን ማበረታታትና ድጋፍ ማድረግ ህገወጥ መሆኑን እና የህፃናት ጋብቻን በግልጽ በማወጃቸው ሊከሰሱ እንደሚችሉ እንዲያውቁ ማድረግ፤
- የሴት ልጅ ግርዛት (በተለይም የብልት መቁረጥ) እና የህፃናት ጋብቻ ሰልሚያስከትሉት ጉዳት እንዲሁም ጋብቻን እስከ ጎልማሳነት ዕድሜ ድረስ ማዘግየት ስላለው ጥቅም ትምህርት መስጠት፤
- የሴት ልጅ ግርዛት እና የህፃናት ጋብቻ በእስልምና የተፈቀደ ነው የሚሉ የተሳሳቱ አመለካከቶችንና ልጃገረዶች መስገድ ለመግባትና ለመስገድ መገረዝ አለባቸው የሚለውን አመለካከት ጨምሮ ማስተካከልና ልማዶቹን ለማስቀረት አሳማኝ ሀይማኖታዊ ክርክሮችን ማዘጋጀት፤
- ለልጃገረዶች ለራሳቸው እና ለወደፊት ትውልዶች ሲባል ለሴቶች ልጆች ትምህርት ድጋፍ ማጠናከር፤
- ልጃገረዶችና ሴቶች ለቤተሰባቸውና ለማህበረሰባቸው የሚያበረክቱትን እሴት ዕውቅና መስጠት፣ አዋቂ ወንዶች እና ወንዶች ልጆችን ሴቶች ልጆች ላይ ጥቃት እንዳያደርሱ ከጥቃት እንዲርቁ፣ የሴት ቤተሰብ አባላትን በጥሩ ሁኔታ እንዲይዙ ማስተማር ያለውን ጠቀሜታ ጨምሮ ሰፊውን የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ማስተካከል፤

## ሰዎች ጎጂ ልማዶችን እንዲተዉ ለማበረታታት የጎሳና ባህላዊ መሪዎችን ማሳተፍ

ጎሳና ባህል የአፋር እና የሶማሌ ማንነት ማዕከል ናቸው፤ ለሴት ልጅ ግርዛትና የህፃናት ጋብቻ ቀጣይነት ጭምር። ስለሆነም መንግስታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተዋናዮች ከባህላዊ መሪዎች ጋር ተቀራርበው ልጃገረዶችን እና ሴቶችን የሚጎዱ እምነቶችን እና ተግባራትን መቀየር መጀመር አለባቸው። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል።

- የልጃገረዶችን ትምህርት ማሳደግ፤
- የሴት ልጅ ግርዛት በተለይም ብልት መስፋት ስለሚያስከትለው ጉዳት ግንዛቤ ማሳደግ፤
- የህፃናት ጋብቻን ጉዳትና ጋብቻን እስከ ጎልማሳነት ዕድሜ ማዘግየት ያለውን ጥቅም ግንዛቤ ማሳደግ፤
- ማህበረሰቦች - በተለይም ባህላዊ ቆራጮችና እናቶች - ማንኛውም አይነት የሴት ልጅ ግርዛት ህገ-ወጥና ቅጣት እና እስራት የሚያስከትል መሆኑን እንዲያውቁ ማድረግ።

## የለውጥ መንገዶችን ለመክፈትና እሸናፊዎችን በሁሉም ደረጃ ለመደገፍ ጥረቶችን ማስቀጠልና ማስፋፋት

የህፃናት ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም የኢትዮጵያውያን ህብረት እነዚህን ጎጂ ልማዶች ለማስቀረት የጀመረውን ጥረት በማፋጠን አዳዲስ የለውጥ መንገዶችን በመክፈት በየደረጃው ያሉ አሸናፊዎችን በመለየት መደገፍ አለበት። ይህም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ከክልል ባለስልጣናት ጋር በመስራት የብሄራዊ እና ክልላዊ ህጎችን ማስማማት፤ ከዞንና ወረዳ ኃላፊዎች ጋር በመስራት ግንዛቤን ማሳደግ እና አፈፃፀምን ማሻሻል፤ ከአካባቢ አመራሮች ጋር በመስራት ልማዳዊ ድርጊቶችንና አሠራሮችን ለማስወገድ በቀበሌ ደረጃ ቁርጠኝነትን ማጠናከር መደገፍ፤ እንዲሁም ከሀይማኖትና የጎሳ መሪዎች ጋር የሚመጥኑና ተግባራዊ የሚሆኑ እቅዶችን ማዘጋጀት፤
- ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች (በተለይ ከጤና፣ ከትምህርት እና ፍትህ) ጋር በመሆን የህፃናት ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን መከላከል፣ በመንግስት ሴክተር እቅዶች ውስጥ ሴቶችን በትምህርት ቤት ለማቆየት ጥረቶችን ማጠናከር፣ የልጃገረዶችና የስርዓተ ጾታ ክበባት መስፋፋትን መደገፍ፣ እና የሴት ልጅ ግርዛትን በህክምና ማገዝን መዋጋት፤
- ልጃገረዶችና ተንከባካቢዎቻቸው አድሎአዊ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለመዋጋት አቅም እንዲያገኙ፣ የራሳቸውን ህይወት ለመምራት ያላቸውን አቅም እንዲያውቁ ለመጠቀም፣ ለማነሳሳትና ለመዘገብ ለጋዜጠኞችና የሚዲያ ፕሮዲውሰሮች የአቅም ግንባታ ድጋፍ ማድረግ።

## በጠንካራ የረጅም ጊዜ ግምገማዎች የተጠቆሙትን ሁለቱንም ልማዳዊ ድርጊቶች ለማስቀረት በሚደረገው ጥረት ላይ ኢንቬስትመንትን ማሳደግ

የሴት ልጅ ግርዛትንና የህፃናት ጋብቻን ማስቀረት ብዙ ሃብትን የሚጠይቅና ረጅም ጊዜ የሚወስድ ሂደት በመሆኑ የልማት አጋሮች ኢንቨስትመንቶችን በማስፋፋት በረጅም ጊዜና በቀይጥ ዘዴ የምርምር በማካሄድ ተጽእኖዎችን መገምገም አለባቸው። ይህም የሚከተሉትን ማካተት አለበት:

- በሩቅ ያሉ አርብቶ አደር ማህበረሰቦች ውስጥ ያሉትን ጨምሮ ለሁሉም ህጻናት ትምህርት ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤
- በጣም ተጋላጭ ለሆኑ ቤተሰቦች ማህበራዊ ጥበቃን ማጠናከር፣ በተቻለ መጠን የሴቶችን ትምህርት ለማሻሻልና የህፃናት ጋብቻን ለመቀነስ ማህበራዊ ጥበቃውን ጥቅም ላይ ማዋል፤
- የአካባቢ አገልግሎቶችን ለማሻሻል የክልሎችን አቅምን ማጠናከር፤
- ገዳቢ የሥርዓተ-ፆታ ደንቦችን ለመቀየር በፕሮግራሚንግ ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤
- ለውጦችን ለመከታተል፣ ከአውዱ አንፃር እንዴት በጣም ውሱን የሆኑ ሀብቶችን ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል እና ውጤታማ ፕሮግራሞችን እንዴት ማሳደግ እንደሚቻል ጠንካራ የረጅም ጊዜ ክትትል፣ ግምገማ እና ምርምር ላይ ኢንቨስት ማድረግ ናቸው።

# ማጣቀሻ መጻሕፍት


Central Statistical Agency of Ethiopia (CSA) and ICF (2017) *Ethiopia Demographic and Health Survey 2016*. Addis Ababa, Ethiopia, and Rockville, Maryland, USA: CSA and ICF (https:// dhsprogram.com/pubs/pdf/FR328/FR328.pdf)

Central Statistical Authority/Ethiopia and ORC Macro (2001) *Ethiopia Demographic and Health Survey 2000*. Addis Ababa, Ethiopia: Central Statistical Authority/Ethiopia and ORC Macro (http://dhsprogram.com/pubs/pdf/FR118/FR118.pdf)

Elezaj, E., Ramful, N., Cebotari, V. and De Neubourg, C. (2019) *Gender equality, women's empowerment and child wellbeing in Ethiopia.* UNICEF Ethiopia and Ministry of Women, Children and Youth (www.unicef.org/ethiopia/media/2811/file/ Gender%20Equality,%20Women's%20empowerment%20 and%20child%20wellbeing%20in%20Ethiopia.pdf)

Jones, N., Gebeyehu, Y. and Hamory-Hicks, J. (2019) 'Exploring the role of evolving gender norms in shaping adolescents' experiences of violence in pastoralist Afar, Ethiopia' in D. Bühler-Niederberger and L. Alberth (eds.) *Victim, perpetrator, or what else? (Sociological Studies of Children and Youth, Vol. 25)*. Bingley: Emerald Publishing Limited (https://doi.org/10.1108/S1537-466120190000025008)

Presler-Marshall, E., Jones, N., Dutton, R., Baird, S., Yadete, W., Woldehanna, T., Guday, E. and Gezaghne, K. (2020) *'Girls don't shout if they are raped... that is taboo': exploring barriers to Ethiopian adolescents' freedom from age- and gender-based violence.* London: Gender and Adolescence: Global Evidence (https://www.gage.odi.org/publication/girls-dont-shout-if-they-are-raped-that-is-taboo-exploring-barriers-to-ethiopian-adolescents-freedom-from-age-and-gender-based-violence/)

UNICEF (2020) *A profile of female genital mutilation in Ethiopia*. Addis Ababa, Ethiopia: UNICEF (https://data.unicef.org/resources/a-profile-of-female-genital-mutilation-in-ethiopia/)



የስርዓተ ፆታና ታዳጊነት፡ አለማቀፋዊ መረጃ

ይህ የፖሊሲ ማስታዎሻ የጌጅ የረጅም ጊዜ ጥናት ፕሮግራም አካል ሲሆን የዚህ ጥናት ግኝት ጥምር ጥናት በአየረላንድ ኤምባሲ የገንዝብ ድጋፍ አማካይነት የተሰራ ነው። ይሁን እንጅ በዚህ የፖሊሲ ማስታዎሻ ውስጥ የተጠቀሱት ምልክታዎቸና የተካተቱት መርጃዎቸ የአየረላንድን መንግስት ፖሊሲ አቋም ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም፤ በአየረላንድ መንግስት በኩልም ቅቡልነት አይኖራቸውም። ለእንዲህ አይነት ምልክታዎቸና መርጃዎቸ እንዲሁም ተዛማጅ ጉዳዮቸ የአየረላንድ መንግስት ሀላፊነት አይወስድም።

በዚህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ ውስጥ የተካተቱት መስለ-መረጃዎቸ (infographics) የተዘጋጁት በኦታቪያ ፓስታ ለጌጅ ነው።

ISBN: 978-1-913610-92-0